# አምስቱ አዕማደ ምሥጢር

## በኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሀዋሳ ደ/ም/ቅዱስ ገብርኤል ገዳም መራሔ ድኅነት ሰንበት ት/ቤት



# መክስተ አርዕስት

**ምዕራፍ አንድ ..... 4**
**አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ..... 4**
1.1 ምሥጢር ማለት ምን ማለት ነው? ..... 4
1.2 አዕማድ ማለት ምን ማለት ነው? ..... 4
1.3 አዕማድ ምሥጢር በቁጥር አምስት ስለመሆናቸው ..... 4
1.4 አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ለምን ምሥጢራት ተባሉ? ..... 5
**ምዕራፍ ሁለት ..... 7**
**ምሥጢረ ሥላሴ ..... 7**
2.1 የቃሉ ትርጉም ..... 7
2.2 የሥላሴ ሦስትነታቸው በምንድን ነው? (እንዴት ነው?) ..... 7
2.2.1 የስም ሦስትነት ..... 7
2.2.2 የአካል ሦስትነት ..... 9
2.2.3 የግብር ሦስትነት ..... 11
2.2.4 የኩነት ሦስትነት ..... 13
2.3 የሥላሴ አንድነት ..... 15
2.4 ለምሥጢረ ሥላሴ የሥነ ፍጥረት ምሣሌ ..... 15
2.5 ለምሥጢረ ሥላሴ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ..... 17
**ምዕራፍ ሦስት ..... 20**
**ምሥጢረ ሥጋዌ ..... 20**
3.1 ሥጋዌ ማለት ምን ማለት ነው? ..... 20
3.2 የእግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት ..... 20
3.3 ነገረ ማርያም ..... 22
3.3.1 የእመቤታችን የስሟ ትርጓሜ ..... 23
3.3.2 እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በምሳሌ ..... 24
3.3.3 እመቤታችን ጌታችንን እንደምትወልድ በትንቢት ..... 26
3.4 አምላክ ለምን ሰው ሆነ? ..... 28
3.5 አምላክ እንዴት ሰው ሆነ? ..... 30
**ምዕራፍ አራት ..... 34**
**ምሥጢረ ጥምቀት ..... 34**
4.1 የምሥጢረ ጥምቀት ትርጉም ..... 34
4.2 ጥምቀተ ክርስቶስ ..... 34
4.2.1 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ተጠመቀ? ..... 34
4.2.2 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በሠላሳ ዘመኑ ተጠመቀ? ..... 35
4.2.3 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በዮርዳኖስ ተጠመቀ? ..... 35
4.3 ጥምቀት ለምን በውኃ ይፈጸማል? ..... 36

4.4 የክርስቲያኖች ጥምቀት ..... 37
4.4.1 የሕፃናት ጥምቀት ..... 37
4.4.2 የሕፃናት ጥምቀት ለምን በ40 እና በ80 ቀናት ሆነ? ..... 37
4.4.3 የንዑሰ ክርስቲያን ጥምቀት ..... 37
4.5 ጥምቀት አንዲት ናት ..... 38
**ምዕራፍ አምስት ..... 40**
**ምሥጢረ ቁርባን ..... 40**
5.1 የምሥጢረ ቁርባን ትርጉምና አመሠራረት ..... 40
5.2 አመሠራረት ..... 40
5.3 የምሥጢረ ምሳሌ በብሉይ ኪዳን ..... 41
5.4 የምሥጢረ ቁርባን አገልግሎት /ጥቅም/ ..... 42
5.5 ምሥጢረ ቁርባን በስንዴና በወይን የመሆኑ ምሥጢር ..... 42
5.6 ቅዱስ ቁርባን በመብልና በመጠጥ የሆነበት ምክንያት ..... 43
5.7 ቅዱስ ቁርባን መታሰቢያ ሳይሆን አማናዊ ነው ..... 43
**ምዕራፍ ስድስት ..... 45**
**ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ..... 45**
6.1 የቃሉ ትርጉም ..... 45
6.2 የትንሣኤ ዓይነቶች ..... 45
6.2.1 ትንሣኤ ልቡና ..... 45
6.2.2 ትንሣኤ ዘጉባኤ ..... 46
6.3 የሙታን አነሣስ እንዴት ነው? ..... 46
6.4 ለትንሣኤ ሙታን የተነገሩ ትንቢቶችና ምሳሌዎች ..... 47
6.5 በብሉይ ኪዳን የነበሩ ትንሣኤን እንዴት ያያሉ? ..... 48
6.6 በምን ዓይነት ሁኔታ እንነሣለን? ..... 48
**ማጠቃለያ ..... 51**
**ግለ- ፈተና (ራስን የመመዘኛ )ጥያቄዎች ..... 52**

# ምዕራፍ አንድ
# አምስቱ አዕማደ ምሥጢር



## መግቢያ

ውድ ተማሪያችን በዚህ ትምህርት ውስጥ የምንመለከተው ስለ አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ለምን ‹ምሥጢርና›፣ ‹አዕማድ› ተባሉ የሚለውን ነው።

## ዓላማዎች

ይህን ምዕራፍ በሚገባ አጥንተው ከጨረሱ በኋላ:-

- ‹ምሥጢር› ምን ማለት እንደሆነና የፈጣሪና የፍጡራንን ምሥጢር አንድነትና ልዩነት ያስረዳሉ፤ እንዲሁም
- አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ለምን አምስት እንደሆኑና አዕማድ (ምሰሶ) የተባሉበትን ምክንያት ያብራራሉ።

## 1.1 ምሥጢር ማለት ምን ማለት ነው?

ውድ ተማሪያችን ምሥጢር የሚለው ቃል ***ለመሠጠረ*** (አመሠጠረ) ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙ ሰወረ፣ ደበቀ፣ አረቀቀ ማለት ነው። ምሥጢር በሁለት ይከፈላል እነርሱም የፈጣሪ ምሥጢርና የፍጡራን ምሥጢር ይባላሉ፡-

- **የፈጣሪ ምሥጢር፡-** ማለት ከፍጡራን ዕውቀትና ሕሊና በላይ የሆነ፣ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የማያውቀው፣ በራሱ በባለቤቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገለጥ የሚታወቅ ማለት ነው።
- **የፍጡራን ምሥጢር፡-** የሚባለው ደግሞ አዋቂዎች በሆኑት የመላእክትና የሰው ልጅ ምሥጢር በመባል የሚታወቅ ነው።
    - የመላእክት ምሥጢር የሰው ልጅ እግዚአብሔር የገለጠለትን ያህል የሚያውቀው የሚገለጥለት ነው።
    - የሰው ልጆች ምሥጢር የሚታወቅ ከጊዜ በኋላ ይፋ የሚሆን ማለት ነው።

## 1.2 አዕማድ ማለት ምን ማለት ነው?

‹አዕማድ› ማለት ምሰሶዎች ማለት ነው። በነጠላ ስንመለከተው ደግሞ ‹ዓምድ› ይሆናል፤ ትርጉሙም ምሰሶ፣ ቋሚ ማለት ነው። የምሰሶ ጥቅሙ አንድን ቤት አጽንቶ ማቆም ነው። አዕማደ ምሥጢርም አንድን ክርስቲያን በሃይማኖቱ አጽንተው የሚያቆሙ ናቸውና። አንድም ዓምድ ለጽሕፈት ሲሆን ደግሞ ለገጽ ስፋት መክፈያነት ያገለግላል። ለንባብ መመጠኛ ነው። እንዲሁም ባሕርየ ሥላሴን ከመጠን አልፈን እንዳንመረምር የሚገድብ በመሆኑ የተሠጠ ስያሜ ነው።

## 1.3 አዕማድ ምሥጢር በቁጥር አምስት ስለመሆናቸው

አዕማደ ምሥጢር አምስት መሆናቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ እናገኛዋለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- *“ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና፤ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፤ ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ*

*አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሣን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወድዳለሁ"* 1 ቆሮ፡-14÷18-19 በማለት ተናግሮአል። አምስት ቃላት ያለው አምስቱ አዕማደ ምሥጢራትን እንደሆነ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ያስረዳሉ።

## 1.4 አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ለምን ምሥጢራት ተባሉ?

- የመጀመሪያው ለማያምኑ የማይነገር (የተሠወረ) ምሥጢር ስለሆነ ነው። ለሚያምኑ ግን የተገለጡ፣ የተሠጡ ምሥጢራት ናቸው። *"በእግራቸው እንዳይረግጡት፤ ተመልሰውም እንዳይነክሷቸሁ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፤ ዕንቊዎቻቸሁንም በእርያዎች ፊት አትጣሉ"* ማቴ፡-7÷6 በማለት ተጠቅሷል። ውሾችና እርያዎች የተባሉት የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የማያምኑ አሕዛብና መናፍቃን ናቸው። የተቀደሱ የተባሉትም የቤተክርስቲያን ምሥጢራት ናቸው።
- ሁለተኛው ደግሞ በሥጋዊ አእምሮ ተመራምረብ ልንደርስባቸው ስለማንችል ነው። አዕማደ ምሥጢርን ለማወቅና ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ ጸጋ፣ ርዳታ ያስፈልጋል። *"ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም"* 1 ቆሮ፡-2÷14
- የምውናቃቸው ራሱ እግዚአብሔር የገለጠልን ያህል ስለሆነ ነው።



*አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት የሚባሉት ፡-*

- ምሥጢረ ሥላሴ
- ምሥጢረ ሥጋዌ
- ምሥጢረ ጥምቀት
- ምሥጢረ ቁርባን
- ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው።

ክርስቲያኖች ሁሉ እነዚህን አምስቱ አዕማደ ምሥጢርን ማወቅ አለባቸው። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለሌሎችም ማስተማርና ማሳወቅ አለበት። አዕማድ መባላቸውም ዓምድ (ምሰሶ) አንድን ቤት እንደሚያጸና ሁሉ እነዚህም የምእመናንን ልቦና በሃይማኖት ያጸናሉ፤ ከኑፋቄና ጥርጥር ይጠብቃሉ ያድናሉና። ምሰሶ የሌለው ቤት እንደማይጸና ሁሉ አዕማደ ምሥጢርን ያልተማረ፣ ያላወቀና ያላመነ ሰውም እንዲሁ አይጸናም፤ በኃጢአት፣ በምንፍቅና ይወድቃል፣ ይጠፋል፡ ፡ ከአምስቱ ምሥጢርም አስቀድመን ምሥጢረ ሥላሴን መማር ያስፈልጋል። ቅዱስ ቄርሎስ እንዲህ እንዳለ፡- *‹አስቀድመን የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት እናስተምራለን›*



# መልመጃ አንድ

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ ስጡ**

1) ምሥጢር ማለት ምን ማለት ነው? ስንት ዓይነት ምሥጢራት አሉ?

_____

_____

2) አዕማደ ምሥጢር ለምን አዕማድ ተባሉ?

_____

_____

3) አዕማደ ምሥጢር ለምን ምሥጢር ተባሉ?

_____

_____

4) አዕማደ ምሥጢር የሚባሉትን በዝርዝር አስቀምጡ?

_____

_____

# ምዕራፍ ሁለት
# ምሥጢረ ሥላሴ



## መግቢያ

ውድ ተማሪያችን በዚህ ትምህርት የምናየው ስለ ምሥጢረ ሥላሴ አንድነትና ሦስትነት፣ ለምሥጢረ ሥላሴ ሥነ ፍጥረታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌን ይሆናል። አምላካችን እግዚአብሔር ምሥጢሩን ይግለጥልን አሜን።

## ዓላማዎች

ይህን ምዕራፉ በሚገባ አጥንተው ከጨረሱ በኋላ:-

- ‹ሥላሴ› ምን ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ፤ ‹ቅድስት ሥላሴ› ሲባልስ ምን ማለት ተፈልጎ እንደሆነ ይተነትናሉ፤ እንዲሁም
- የቅድስት ሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ያብራራሉ። በተጨማሪም
- ምሥጢረ ሥላሴን በምሳሌ ደግፈው ያስረዳሉ

### 2.1 የቃሉ ትርጉም

ሥላሴ የሚለው ቃል ‹ሠለሰ› -‹ሦስት አደረገ› ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ሦስትነት፣ ሦስት መሆን ማለት ነው። ምሥጢረ ሥላሴ ማለት ደግሞ ልዩ የሆነ የሦስትነት ምሥጢር፤ የማይመረመር፣ የሰው ልጅ ከሚያውቀው የተለየች ሦስትነት ማለት ነው። ምክንያቱም ሥላሴ አንድ ሲሆኑ ሦስት፤ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸውና።



*ይህንንም ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ* ሲናገር *“እንዘ አሐዱ ሠለስቱ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ፤ ይሜልሱ በአካላት ወይትዋሐዱ በመለኮት፤ አንድ ሲሆኑ ሦስት፤ ሦስት ሲሆኑ አንድ፤ በአካላት ሦስት ሲሆኑ በመለኮት አንድ የሚሆኑ”* በማለት ተናግሮአል።

ታዲያ ሥላሴ አንድም ሦስትም ናቸው ስንል የሥላሴ ሦስትነትና አንድነት በምን በምንድን ነው? ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

### 2.2 የሥላሴ ሦስትነታቸው በምንድን ነው? (እንዴት ነው?)

የሥላሴ ሦስትነታቸው ወይም ሦስት መሆናቸው በምንድን ነው? (እንዴት ነው?) ቢሉ ሥላሴ በስም፣ በአካል፣ በግብር እና በኩነት ሦስት ናቸው።

#### 2.2.1 የስም ሦስትነት

የስም ሦስትነት ማለት ሥላሴ በሦስትነት የሚጠሩበት ስም ማለት ነው፤ ይኸውም አብ፤ ወልድ፤ መንፈስ ቅዱስ የአካል ስም ወይም አካላቸው የሚጠራበት ስም ነው።

ወላዲ፣ አሥራጺ፤ ተወላዲ፤ ሠራጺ የሚለው ደግሞ የግብር ስም፤ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ የሚለው ደግሞ የኩነት ስም በመባል ይታወቃል። እነዚህን ስሞች ሥላሴን በሦስትነት የምንጠራበት ነው። ሥላሴን በአንድነት ደግሞ የምንጠራበት ስም እግዚአብሔር፤ አምላክ፤ ፈጣሪ፤ አዶናይ... እያልን ነው።

ውድ ተማሪያችን በሥላሴ ዘንድ የስምና የግብር ተፋልሶ የለም። ይህ ማለት የስም መቀያየር የለባቸውም ምክንያቱም ስማቸው ግብራቸው ስለሚገልጽ ነው።

- ***አብ፡-*** አብ እንጂ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አይጠራም፤ የእግዚአብሔር አብ ስም ከሦስቱ አካላት አንዱ አብ ብቻ የሚጠራበት ስም ነው፤ አብ ማለት አባት ማለት ነው።

- ***ወልድ፡-*** ወልድ እንጂ አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተብሎ አይጠራም፤ የእግዚአብሔር ወልድ ስም ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ብቻ የሚጠራበት ስም ነው፤ ወልድ ማለት ልጅ ማለት ነው።

- ***መንፈስ ቅዱስ፡-*** መንፈስ ቅዱስ እንጂ አብ ወይም ወልድ ተብሎ አይጠራም፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም ከሦስቱ አካላት አንዱ መንፈስ ቅዱስ የሚጠራበት ስም ነው። መንፈስ ቅዱስ ማለት ሠራጺ (የሚወጣ)፣ አጽናኝ ማለት ነው።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል። ይህንንም በመቀጠል እንመለከታለን። ቅዱስ ማቴዎሰ በወንጌሉ ላይ *"እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፤ የዘዝኋችሁንም እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው"* ማቴ፡-28÷19 በማለት የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ስም ጠቅሷል።

## እግዚአብሔር አብ የሚጠራበት ስም

*"እነሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ ይህ ነው አለ"* ማቴ፡-3፣17 በማለት አብ በሰማይ ሆኖ እንደተናገረ፤ *‹በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ›* በማለት ደግሞ ወልድን ጠቅሶታል። በሌላም ቦታ *" ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብጹዕ ነህ"* ማቴ፡-16፡17 ብሎ ‹አባቴ› በማለት አብን ጠቅሷል *"አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣልኛል፤ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም"* ዮሐ፡-6፣36

## *እግዚአብሔር ወልድ በብሉይ ኪዳን የሚጠራበት ስም*

***ቃል፡-*** *‹‹በመጀመሪያው ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ››* ዮሐ፡-1፡1 በማለት ቅዱስ ዮሐንስ የወልድን ቀዳማዊነት ቃል በሚለው ስም ገልጾታል። ቅዱስ ዳዊት ስለ ወልድ ቃልነት ሲናገር፡- *‹‹የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች፤ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ››* መዝ፡-32፣5-6 በማለት ወልድን የእግዚአብሔር ቃል ብሎ ጠርቶታል።

***እንዲሁም፡-*** *የእግዚአብሔር እጅ፣ ኃይል፣ ጥበብ፣ ብርሃን እና ሎጎስ በመባል በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠርቶዋል።*

***እግዚአብሔር ወልድ በሐዲስ ኪዳን የሚጠራበት ስም***

- **አማኑኤል** *“... እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች”* ኢሳ፡-7፤ 14 በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ የወልድ ስም ከተዋሕዶ በኋላ አማኑኤል እንደሚባል ተናግሮአል።
ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስም የኢሳይያስን ትንቢት በመጥቀስ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- *‹‹በነቢይ ከጌታ ዘንድ፡- እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፤ ትርጓሜውም፡- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው››* ማቴ፡-1፡22 በማለት ወልድ አማኑኤል እንደሚባል ጽፏል።

- **ኢየሱስ** (መድኃኒት) ማለት ነው። *“... እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ”* *ማቴ፡-1፡21* *“መልአኩም እንዲህ አላት፡- ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ፤ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ”* ሉቃ፡-1፡30-31 እነዚህ ጥቅሶች የሚያመለክቱን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ እንደሚባል የሚያስገነዝቡ ናቸው።

- **ክርስቶስ** *“መልአኩም እንዲህ አላቸው፡- እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና”* ሉቃ፡-2፤10-11

  የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ከሦስቱ አካላት የአንዱ የመንፈስ ቅዱስ ስም ነው።

**መንፈስ ቅዱስ የሚጠራባቸው ስሞች**

- **መንፈስ** *“ኢየሱስም መለሰ፤ እንዲህ ሲል፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም”* ዮሐ፡-3፤5 “የጸጋም ሥጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው።” 1 ቆሮ፡-12፤4
- **የእግዚአብሔር መንፈስ** *“የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ነበር”* ዘፍ፡-1፤2 *“....አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል”* ኢሳ፡-48፡16
- **አጽናኝ (ጰራቅሊጦስ)** *“ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል››* ዮሐ፡-15፡26 *“....እኔ ባልሔድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና...”* ዮሐ16፣7

## 2.2.2 የአካል ሦስትነት

የሥላሴ ሦስትነት ከሚገለጥባቸው ነገሮች አንዱ የአካል ሦስትነት ነው። ሥላሴ በአካል ሦስት ናቸው *‹‹እንዘ ይሜለሱ በአካላት ወይትዋሐዱ በመለኮት ... በአካል ሦስት ሲሆኑ በመለኮት አንድ ለሚሆኑ››* ተብሎ በአካላት ሦስት በመለኮት አንድ መሆናቸው ተገልጿል።

የሥላሴን የአላት ሦስትነት ለመረዳት ‹አካል› ምን እንደሆነ መረዳት ቀዳሚ ተግባር ነው። አካል ማለት ሰውነት ወይም ሥጋ ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም አብና መንፈስ ቅዱስ ሥጋን አልተዋሐዱምና። አካል ማለት (በመጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ-አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ ገጽ-218) እኔ የሚል ህላዌ፣ ነባቢ፣ በቁሙ ቀመና፣ የባህርይ፣ የግብር፣

የስም ባለቤት እገሌ የሚባል። እኔ ማለትም የሚገባ ዕውቀት ቀዋሚነት ላላቸው ለማይሞቱና ለማይጠፉ ለሦስቱ ብቻ። ‹ለአምላክ፣ ለመልአክ፣ ለነፍስ ብቻ›። ‹አካል› ባልን ጊዜ እኔነት፣ ቅርጽ፣ ቁመት፣ አኗኗር ማለታችን ነው። ከዚሁ ጋር መገንዘብ የሚገባን ነገር አካል በሁለት ይከፈላል፤ የሚታይ አካልና የማይታይ አካል ተብሎ ነው። ከዚህ አንጻር የሥላሴ አካል የማይታይ፣ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ ነው። እንደሰው አካል የሚጨበጥ፣ የሚወሰን ግዙፍ አይደለም፤ አካላቸው ምሉዕ፣ ረቂቅ፣ ስፉሕ ነው እንጂ። ምሉዕነታቸውና ረቂቅነታቸው እንደምን ነው? ቢሉ፡-

**ምሉዕነታቸው፡-** ከአርያም በላይ ቁመቱ፣ ከበርባሮስ በታች መሠረቱ፣ ከአድማስ እስከ አድማስ ስፋቱ፣ ተብሎ አይነገርለትም፤ አይመረመርም። ሥላሴ ዓለሙን ይወስኑታል እንጂ ዓለሙ ሥላሴን አይወስነውም። አባ ሕርያቆስ እንዲህ ብሎ እንደተናገረ፡-

> *“**አኮ ዘበቱ ለመለኮት ምስፋሕ**”* ለመለኮት የሚሮጥበት ሜዳ፣ የሚሸልክበት ቀዳዳ፣ የሚገባበት ዋሻ፣ የሚመክተው ጋሻ፤ አንድም የሚገኝበት አዳራሽ፣ የሚሰወርበት እልፍኝ ያለው አይደለም፤ አንድም እንደራስ፤ እንደ ደጃዝማች፤ እንደ ቢትወደድ፤ ያለ ሰፊ ግዛት፣ ዳሩ እሳት መሐሉ ገነት ተብሎ የተከለለ እንደ ቀኛዝማች እንደ ግራዝማች ያለ ጠባብ ግዛት ያለው አይደለም።
>
> ***...አለ ውስተ ክርሉ በሓውርት መለኮቱ››*** ጌትነቱ በአራቱ ማዕዘን ምሉዕ ነው እንጂ፤ አንድም ጌትነቱ ከደረሰበት መልቶ ይኖራል እንጂ። ***‹‹አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ዘበላዕሉ ጠፈር ወዘበታሕቱ መሠረት ...*** ለመለኮት ከላይ ጠፈር ከታች መሠረት ያለው አይደለም። ጠፈሩም መሠረቱም እርሱ ነው እንጂ፤ አንድም ከላይ ጽርሐ አርያም ከታች በርባኖስ አይወስነውም፤ ጽርሐ አርያምን በርባኖስን እርሱ ይወስነዋል እንጂ።

**ረቂቅነታቸው፡-** እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ስለዚህ መንፈስ ማለት የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ የማይያዝ ማለት ነው። እንኳን እግዚአብሔር እርሱ የፈጠራቸው መላእክት፣ የሰው ነፍስ፣ ረቂቃን ናቸው። በዚህ ዓለም ነፋስ ረቂቅ ነው፣ ከነፋስ ደግሞ የሰው ነፍስ ረቂቅ ናት፣ ከሰው ነፍስ መላእክት ረቂቃን ናቸው፤ ከመላእክት ደግሞ እግዚአብሔር ረቂቅ ነው። መላእክት በእግዚአብሔር ዘንድ እንደተራራ የገዘፉ ናቸው።

*“ከመንፈስህ ወዴት እሔዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲዖልም ብወርድ በዚያ አለህ፤ እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር በዚያ እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝህም ትይዘኛለች። በውኑ ጨለማ ትሸፍነኛለች ብል ሌሊት በዙሪያዬ ብርሃን ትሆናለች፤ ጨለማ ከአንተ ዘንድ አይጨልምምና ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለችና...”* መዝ፡-138፣7-11 በማለት የእግዚአብሔርን ረቂቅነትና ከእርሱ ምንም እንደማይሰወር ተናግሮአል።

ታዲያ ይህ የማይታየው የማይጨበጠው የሥላሴ አካል በተከፍሎ ልዩ በሆነች ሦስትነት የጸና አካል ነው። ይህ ማለት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የራሳቸው የሆነ ገጽ አካል አላቸው ማለት ነው።

- አብ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም አካል አለው
- ወልድም ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም አካል አለው
- መንፈስ ቅዱስም ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም አካል አለው

ሥላሴ በአካል ሦስት ስለሆኑ በአብርሃም ዘመን ለራሱ ለአብርሃም ተገልጸውለታል። *"በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት፤ ዓይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ...."* ዘፍ፡-18፣1-15 ሥላሴ ለወዳጃቸው ለጻድቁ አብርሃም በአንድነትና በሦስትነት ተገልጸውለታል። ሌላው በሐዲስ ኪዳን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕረ ዮርዳኖስ ሲጠመቅ አብ በተለየ አካሉ *‹የምወድደው ልጄ ይህ ነው›* በማለት ሲመሰክር ወልድ በተለየ አካሉ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ፤ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሣል ከላይ ሲወርድ ምሥጢረ ሥላሴ ተገልጧል። ማቴ፡-3፤13-17 ይህም የሚያሳየን ሥላሴ በአካል ሦስት መሆናቸውን ነው።

### 2.2.3 የግብር ሦስትነት

ሥላሴ በግብር ሦስት ናቸው ስንል በአካላት ግብር ማለት ነው። የአካል ግብር ማለት ወላዲነት አሥራጺነት፣ ተወላዲነትና፣ ሠራጺነት ናቸው።

- የአብ የአካሉ ግብር (ሥራ)፡- ወልድን መውለድ፣ መንፈስ ቅዱስና ማሥረጽ ነው።
- የወልድ የአካሉ ግብር (ሥራ)፡- ተወላዲ (መወለድ) ነው፤ የሚወለደውም ከአብ ብቻ ነው።
- የመንፈስ ቅዱስ የአካሉ ግብር (ሥራ)፡- መሥረጽ (መውጣት) ነው፤ የሚሠርጸውም ከአብ ብቻ ነው።

ከላይ የተጠቀሰውን ወለደ፣ አሠረጸ እና ተወለደ፣ ሠረጸ የሚባሉትን ቃላት በዕለት ተዕለት ኑሮአችን እንደምንጠቀምባቸው የቋንቋ አገባብ ለሥላሴም የምንጠቀምበት ከሆነ ከስህተት ውስጥ ይጨምረናል። ታዲያ አብ ወልድን ወለደው መንፈስ ቅዱስን አሠረጸው ስንል ምን ማለታችን ነው*?* ከዚህ በመቀጠል እንመለከተዋለን።

መጽሐፍ ቅዱስ የአብን ወላዲነትና አሥራጺነት፣ የወልድን ተወላዲነት፣ የመንፈስ ቅዱስን ሠራጺነት በግልጽ አሥፍሮት ይገኛል። የገለጸውም ‹ጸአት› ወይም ‹መውጣት› በሚለው ተመሳሳይ ቃል ነው። ለምሳሌ፡-

- ስለ አብ ወላዲነትና ስለወልድ ተወላዲነት (አወጣጥ) ሲናገር *‹‹ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቼአለሁ››* ዮሐ፡-16÷28 በማለት በዮሐንስ ወንጌል ተጠቅሷል።
- ስለ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺነትና ስለ አብ አሥራጺነት ደግሞ ሲናገር *‹‹ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ ...››* ዮሐ፡-15÷26 በማለት በተመሳሳይ ሰፍሮ እናገኛለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ‹መውጣት› በሚል ተመሳሳይ ቃል ያስቀመጠውን የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣት ፤ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ልዩነቱን አስቀምጠውታል። ይኸውም የወልድን ከአብ መውጣት ‹ተወላዲነት›› ሲሉት የመንፈስ ቅዱስን ከአብ መውጣት ‹ሠራጺነት› በሚል ጠርተውታል።

ተወላዲነትና ሠራጺነት በሚል ቃል መለየት ያስፈለገው በሁለቱም መካከል ሰፊ የምሥጢር ልዩነት ያለ በመሆኑ ነው። የአወጣጣቸው አንድነትና ልዩነት እንደሚከተለው ነው።

- **አንድነቱ**፡- ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሁለቱም ከአብ በመውጣታቸው በአንድ ዓይነት ቃል ጸአት (መውጣት) በሚል የሚገለጽ ነው።

- **ልዩነቱ፡-** ደግሞ የአወጣጣቸው ሁኔታ ነው። ይኸውም ወልድ ከአብ የወጣው በተወላዲነት (በልጅነት) ሲሆን የመንፈስ ቅዱስ ደግሞ በሠራጺነት (በእስትንፋስነት) በመሆኑ ነው። ወልድ ተወላዲ እንጂ ሠራጺ አይባልም፤ መንፈስ ቅዱስም ሠራጺ እንጂ ተወላዲ አይባልም። ይህ ልዩነቱ ነው።

ወልድ ከአብ ተወለደ ተገኘ ሲባል ምሥጢሩን ትተን በጥሬው ልንረዳው አይገባም። ታዲያ ወልድ ተወለደ ብላ ቤተክርስቲያን ስታስተምር አብን አህሎ፣ አብን መስሎ፣ ባለመቀዳደም፣ ባለመከፋፈል እና ባለመለያየት ከባሕርይው ተገኘ (ተወለደ) ማለት ነው። ተወለደም ሲባል በመልክ ይመስለዋል፣ በክብር ይተካከለዋል ማለት ነው። እዚህ ጋር ማስተዋል የሚገባን ሁለት ነገሮች አሉ፤ እነርሱም የመጀመሪያው በመለኮቱ መለያየት ሳይኖር ነው። ሁለተኛው እንደሰው ሥርዓት ያለመቀዳደም ያለመለየትና ያለመከታተል ነው። እንደሰው ሥርዓት ለእኛ መገኘት የእናትና የአባታችን ከእኛ አስቀድመው መገኘት እንደሚኖርባቸው ለአብና ለወልድ እንደዚህ አይደለም፤ ለመኖራቸው መቀዳደም የለባቸውም።

**ቅዱስ አትናቴዎስ**፡- የወልድን ከአብ መወለድ በምንጭና በወንዝ መስሎ ተናግሮአል። ወንዝ ከምንጭ እንደሚገኝና ሁለቱ የተለያዩ እንደሆኑ ነገር ግን ሁለቱም ሁለት ስም ያላቸውና ሁለት የሚታዩ ነገሮች እንደሆኑ ሁሉ አባት ልጅ አይደለም ልጅም አባት አይደለም። አብ የልጁ (የወልድ) አባት ብቻ ነው። ወልድም የአብ ልጁ ብቻ ነው።

**የመንፈስ ቅዱስ ሠራጺነት** (የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣትን ወይንም መሥረጽን ደግሞ እንመልከት) አስቀድመን የመንፈስ ቅዱስ የአካሉ ግብር (ሥራ) ከአብ ብቻ መውጣት (መሥረጽ) ነው ብለናል። አበው ሊቃውንት በመጽሐፍ ቅዱስ ‹መውጣት› በሚል የሠፈረውን የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣት የሚያመለክተውን ቃል ‹መሥረጽ› ብለው እንደሰየሙት አይተናል።

ሠራጺ የሚለው ቃል ሠረጸ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙ ወጣ፣ በቀለ፣ ተገኘ ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ወጣ (ሠረጸ) ሲባል የባሕርይ ጸአት ነው፤ ማለትም ያለመከፈል፣ ያለመለያት (ያለተከፍሎ፣ ያለተመትሮ) እንዲሁም ያለመቀዳደምና ያለመከተል ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሠረጸ ሲባል ከአብና ከወልድ ለዓይን ጥቅሻ ያህል እንኳን ሳይቀድምና ሳይዘገይ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል ክብር ያለው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሠራጺነት ሲናገር *‹‹ከአብ የሚወጣው የእውነት መንፈስ…››* ዮሐ፡-15፥26 ብሎታል። ሊቃውንት የወልድን ከአብ መወለድ ከፀሐይ በሚወጣ ብርሃን እንደመሰሉት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ከአብ መሥረጽ ደግሞ ከፀሐይ በሚወጣ ሙቀት መስለውታል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በፀሐይ ሙቀት ተመስሏል ማለት ነው። በፀሐይ፣ በብርሃኑ እና በሙቀቱ መካከል መለየትና መከፈል፤ መቅድምና መከተል የለም።

> *ጸሎተ ሃይማኖት እንዲህ ብሎ እንደሚናገር ‹‹ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሠረጸ እም አብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት … በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፤ እርሱ ጌታ ሕይወትን የሚሰጥ ከአብ የሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለን እርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረ ነው…›› ተብሎ እንደተጻፈ።*

በሥላሴ ዘንድ ቀደም ብለን እንዳየነው የስምና ግብር ተፋልሶ የለም፤ ወይም በአካላት ግብር ላይ መቀያየር የለም።

- አብ ወልድን ቢወልደው መንፈስ ቅዱስን ቢያሠርጽ እንጂ እንደ ወልድ ተወላዲ (መወለድ) እንደ መንፈስ ቅዱስ መሥረጽ የለበትም ወይም አይወለድም፤ አይሠርጽምም።
- ወልድም፡- ቢወለድ እንጂ እንደ አብ አይወልድም፤ አያሠርጽም። እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሠርጽም።
- መንፈስ ቅዱስም ቢሠርጽ እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርጽም እንደ ወልድም አይወለድም።

ይህንንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ሲያስተምር እንዲህ ሲል ተናግሮታል፡- *‹‹ከአባቴ ከአብ የሚወጣ አጽናኝ መንፈስ››* እያለ ተናግሮአል።
ሥላሴ በአካለት ግብር ሦስት መሆናቸው እንረዳለን፤ እዚህ ላይ ግን አብ ወልድን ወለደው መንፈስ ቅዱስን አሠረጸው ማለት እንደ ሰው ሰውኛ እኛ ለመገኘት የእናትና የአባታችን ቀድሞ መገኘት እንደሚያስፈልግ አይደለም። ይህ ከዚህ ፍጹም የተለየ ምሥጢር ነው።

አብ ወልድን ስለወለደ መንፈስ ቅዱስን ስላሠረጸ ከአብና ከወልድ በፊት ነበር አይባልም፤ ለምሳሌ፡- ፀሐይ ስትወጣ አካሏ፣ ብርሃንዋና ሙቀቷ እኩል እንደሚወጡ ማለት ነው፤ በሥላሴ ዘንድ መቀዳደም የለም ይህንንም አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ላይ እንዲህ ሲል ተናግሮአል።

> ‹‹አብርሃም በፍጥረታዊ ሥርዓት ከይስሐቅ እንዲበልጥ እንደሚቀድም፤ ይስሐቅ ከያዕቆብ እንደሚበልጥ እንደሚቀድም አይደለም፤ ለመለኮት እንዲህ አይደለም። አብርሃም ከልጁ ከይስሐቅ እንደሚበልጥ እንደሚቀድም አብ ከልጁ (ከወልድ) የሚበልጥ የሚቀድም አይደለም፤ ይስሐቅም ከያዕቆብ እንደሚቀድም እንደሚበልጥ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ የሚበልጥ የሚቀድም አይደለም። ያዕቆብ ከይስሐቅ እንዲያንስ ወደኋላ እንደሚሆን መንፈስ ቅዱስም ከወልድ አያንስም ወደኋላ አይሆንም፤ ይስሐቅም ከአብርሃም እንዲያንስ ወደኋላ እንዲሆን ወልድም ከአብ ወደ ኋላ አይሆንም አያንስም።

### 2.2.4 የኩነት ሦስትነት

ምሥጢረ ሥላሴን ለመረዳት የሥላሴን ኩነት መረዳት የማዕዘን ድንጋይ ነው። ምክንያቱም የኩነት ምሥጢር ተዋሕዶተ ሥላሴ የሚታወቅበት ወይም የሥላሴ አንድነት የሚታወቅበት፣ የመገናዘብ ምሥጢር ያለበት እና ተጋብዖ በተከፍሎ፣ ተከፍሎ በተጋብዖ ማለት አንድነት ሳለ መለያየት መለያየት ሳለ አንድነት ያለበት ትምህርት በመሆኑ ነው። እነዚህን ነገሮች በዝርዝር ለማየት ከመሞከራችን በፊት ኩነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንመለከታለን።

**ኩነት** ማለት **‹መሆን›** ወይም **‹መባል›** ማለት ነው። ለምሳሌ ከዊነ ልብ፣ ከዊነ ቃል፣ ከዊነ እስትንፋስ ሲል ልብ መሆን ወይም መባል፣ ቃል መሆን ወይም መባል፣ እስትንፋስ መሆን ወይም መባል ማለት ነው። ስለዚህ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ሦስቱ አካላት ሥላሴ የሚጠሩበት የኩነት ስም ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ ሥላሴ (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) በኩነታት ሦስት ናቸው እንላለን። የአብ ኩነት ልብነት ነው፣ የወልድ ኩነት ቃልነት ነው፣ የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስነት ነው። በዝርዝር ከዚህ በመቀጠል እንመልከት።

- የአብ ኩነት ልብ (ልብነት) ሲሆን በራሱ ለራሱ ልቡና አእምሮ ነው። ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልቡናቸው (ማወቂያቸው) ነው፤ ከእርሱ ሌላ ልቡና የላቸውም።
- የወልድ ኩነት ቃል (ቃልነት) ሲሆን በራሱ ለራሱ ቃል ነው። ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው (መናገሪያቸው) ነው። ከእርሱ ሌላ ቃል የላቸውም።
- የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስ (ሕይወትነት) ሲሆን በራሱ ለራሱ ሕይወት ነው። ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው (ሕይወታቸው) ነው። ከእርሱ ሌላ ሕይወት የላቸውም።

## ኩነታት በመጽሐፍ ቅዱስ

የሥላሴ ኩነት በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ስፍራ ተጠቅሷል። አብ ልብ (ማወቂያ እውቀት)፤ ወልድ ቃል (መናገሪያ)፤ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ (ሕይወት) እንደሆነ በማያሻማ መልኩ የተቀመጠ ትምህርት ነው።

**የአብ ኩነት ልብነት ስለመሆኑ** *‹‹የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘለዓለም ይኖራል፤ የልቡም (የአብ) አሳብ ለልጅ ልጅ ነው››* መዝ፡-32፥11 በማለት የአብ ኩነት ልብነት (አዋቂነት) እንደሆነ ተገልጿል።

**የወልድ ኩነት ቃል ስለመሆኑ** ደግሞ *‹‹በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ››* መዝ፡-32፥6 *‹‹ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ››* ዮሐ፡-1፥14 *‹‹ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ ...››* ዕብ፡-11፥3 በማለት የእግዚአብሔር ወልድ ኩነት ቃል መሆኑን መመልከት እንችላለን። ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ የወልድን ኩነት ስሙ ቃል እንደሆነ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡- *‹‹ ... ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሏል›› ራእ፡-19፥13* ብሎ ገልጾታል።

**የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስነት መሆኑን** በተመለከተ ክቡር ዳዊት *‹‹በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ››* መዝ፡-32፥6 ብሎ ተናግሮአል። ኢዮብም *‹‹እርሱ ልቡን ወደ ራሱ ቢመልስ፣ መንፈሱንና እስትንፋሱን ወደ ራሱ ቢሰበስብ፤ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት ይጠፋል››* ኢዮ፡-34፥14 በማለት የመንፈስ ቅዱስ ከዊን እስትንፋስነት (ሕይወት) ተናገረ።
እስከ አሁን ድረስ ኩነት ምን እንደሆነ እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዴት እንደተቀመጠ አይተናል። ይሁንና የሥላሴ ኩነት ነገር ሰፋ ያለና በደንብ ሊረዱት የሚገባ ስለሆነ ለመረዳት ይመች ዘንድ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ነፍስ ከኩነት ጋር ያላትን ተዛምዶ ወይም ምሳሌነት ያስረዱበትን ትምህርት እንመለከታለን። ይህን መመልከት በጣም ተገቢ ነው፤ እዚህ ላይ ግን መረዳት የሚገባን ነፍስ ለኩነት ምሳሌ ናት ሲባል ምሳሌ ምሳሌ ዘየሐፅፅ (ጉድለት ያለበት ምሳሌ) ናት። ምክንያቱም በነፍስ ኩነት መገናዘብ የለም በሥላሴ ላይ ኩነት ግን በተገናዝቦ (ተዋሕዶን ገንዘብ ያደረገ) ነው።

የነፍስን ምሳሌነቷን ስንመለከት፡-

- የስም ተመሳሳይነት፡- የነፍስ ኩነታት (ጠባይዓት) ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ይባላሉ። የሥላሴም ኩነታት ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ተብለው ይጠራሉ።
- ነፍስ በአካልዋ አንድ ስትሆን በኩነት ግን ሦስት ናት። በዚህም ለሥላሴ አንድነት እና ሦስትነት ምሳሌ ትሆናለች።
- የነፍስ ኩነታት (ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ) ሕልውናቸው (መገኘታቸው) ቅደም ተከተል የሌለበት ነው። ለሥላሴም ኩነት ቃል እና እስትንፋስ ከአብ ሲወጡ ያለ ቅደም ተከተል ነው። በዚህም ምክንያት *‹አሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ›* የሥላሴ ቅድምና አንዲት ናት ተብሎአል በሃይማኖተ አበው።

## 2.3 የሥላሴ አንድነት

አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ስለ ሦስትነታቸው ከገለጸ በኋላ ስለ አንድነታቸው ሲናገር *"አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ በአካል ሦስት እንደሆኑ በባሕርይ ሦስት ብለን የምናምን አይደለም በአካል ሦስት ብለን በባሕርይ አንድ ብለን እናምናለን እንጂ"* በማለት ተናግሮአል።

 አንድነታቸው በምንድን ነው?

_____

_____

ውድ ተማሪያችን: ሥላሴ በስም፣ ግብር፣ በአካል እና በኩነት ሦስት እንደሆኑ ተመልክተናል። አንድነታቸውንም ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

### 2.3.1 በባሕርይ

(ለባሕርዩ መነሻ ምክንያት የለውም፤ የገዛ ራሱ ለራሱ ባሕርይ ነው) እግዚአብሔር ባሕርዩ ቅዱስ ነው ስንል አብ ቅዱስ ነው፣ ወልድ ቅዱስ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ቅዱስ ነው ማለታችን ነው። ኢሳ፡-6፣3

### 2.3.2 በመለኮት

አምላክነትን፣ መፍጠርን፣ ገዢነትን፣ በፈቃድ አንድ መሆንን የሚገልጽ ነው። አባ ሕርያቆስ ሲናገር መለኮትስ ማለት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው በማለት ተናግሮአል።

### 2.3.3. በአገዛዝ

በአራቱ መዓዘን ሙሉዕ በመሆን መግዛት ማለት ነው። "ፍጥረቶቹ ሁሉ በግዛቱ ሥፍራ ሁሉ እግዚአብሔርን ባርኩ፤ ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ" መዝ፡-102፡22

## 2.4 ለምሥጢረ ሥላሴ የሥነ ፍጥረት ምሣሌ

ምንም እንኳን እግዚአብሔርን ከባሕርዩ ልዕልና የተነሣ በምንም ዓይነት ምሳሌ ሊገለጽ ባይችልም *‹‹እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላቸሁ?››* ኢሳ፡-40፣18 ብሎ ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረ ከማይነገር ፍቅሩና ከሚያስደንቅ ትሕትናው የተነሣ ደግሞ ራሱን በተለያዩ ነገሮች መስሎ ሲናገር እናገኛለን። ራሱ አምላካችን እግዚአብሔር በፈቀደልን መልኩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም በልዩ ልዩ ምሳሌዎች መስለው አስተምረዋል። እነዚህም ምሳሌዎች ፍጹም ስላልሆኑና እግዚአብሔርን በሙላት ሊገልጽ የሚችል ምሳሌ የሌለ በመሆኑ ምሳሌ ዘየሐፅፅ ወይም ጉድለት ያለበት ምሳሌ እየተባሉ ይጠራሉ።

 **ነፍስ** ነፍስ በአካሏ ከሦስት የማትከፈል አንዲት ስትሆን ሦስት ኩነታት አሏት፤ ሥላሴም በአገዛዝ፣ በመለኮት፣ በባሕርይ አንድ ቢሆኑም በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት ናቸው።

ቀደም ብለን እንዳየነው የሥላሴ ኩነታት ልብነት፤ ቃልነት፣ እስትፋስነት ሦስትነታቸው ባሕርያቸውን ለሦስት እንደማይከፍለው ነፍስም አካሏ አንድ ቢሆንም ኩነቷ አንድ አካሏን ለሦስት አይከፈለውም። የልብ ከዊነት ልብነት እስትንፋስነትና ቃልነት ነው።

**ሀ)የልብ ከዊን**፡- ከቃልነትና ከእስትንፋስነት ሳይለይ ከራሱ ከዊን ሳይለይ ከሥጋዊ ልብ ጋር ይዋሐዳል።

**ለ) የቃልነት ከዊን**፡- ከልብነቷ፣ ከእስትንፋስነቷ ከዊን ሳይለይ ከራሱ ከዊን ሳይለይ ከሥጋ አንደበት (ምላስ) ጋር ይዋሐዳል።

**ሐ)የእስትንፋስነት ከዊን**፡- ከልብነቷና ከቃልነቷ ከዊን ሳይለይ በራሱ ከዊን ከሥጋ እስትንፋስነት (ከሣንባ ጋር) ይዋሐዳል።

ስለዚህ አንዲት ነፍስ ትባል እንጂ ሦስት አትባልም፤ ሥላሴም (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) አንድ አምላክ ይባል እንጂ ሦስት አምላክ አይባልም።

> **እሳት፡-** እሳት በአካሉ አንድ ሲሆን በባሕርይው ሦስት ከዊን አለው፤ ነበልባል፣ ብርሃን፣ ዋዕይ ናቸው።
> - በነበልባሉ አብ
> - በብርሃኑ ወልድ
> - በሙቀቱ (ዋዕዩ) መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል

ይኸውም መለያየት መከፋፈል ሳይኖርበት በአንድነት የሚኖር ነው፤ እንዲሁ ሥላሴም በአንድነት በሦስትነት ጸንተው የሚኖሩ ናቸው። አባ ሕርያቆስ ይህን ሲናገር፡- *‹‹አብ እሳት ነው ወልድ እሳት ነው መንፈስ ቅዱስ እሣት ነው በልዕልና ያለ አንድ ሕይወትነት ያለው እሳት ነው››* ብሏል። ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ገጽ 147

> **ፀሐይ፡-** በአካሏ አንድ ስትሆን ሦስት ግብራት ያላት ናት፤ ሥላሴም በአምላክነት፣ በአገዛዝ፣ በመለኮት አንድ ቢሆንም በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት ናቸው።
> - በክበቧ (በክብነቷ) አብ
> - በብርሃንዋ ወልድ
> - በሙቀቷ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል

*‹‹ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላቸኋለች››* ኢሳ፡-4፤12 *‹‹የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳላላቸሁ በብርሃኑ እመኑ አላቸው››* ዮሐ፡-12፤36 አባ ሕርያቆስ ስለዚህ ሲናገር፡- *‹‹አብ ፀሐይ ነው፤ ወልድ ፀሐይ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ፀሐይ ነው። ከሁሉም በላይ ያለ አንድ የሕይወት ፀሐይ ነው››* **ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ገጽ 147**

## 2.5 ለምሥጢረ ሥላሴ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ

የተከበሩ ተማሪያችን ስለ ምሥጢረ ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ ተገልጧል። አንዳንድ ሰዎች ‹ሥላሴ› የሚለውን ከጊዜ በኋላ የመጣ ነው ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም ስለ ምሥጢረ ሥላሴ አጉልቶና አስፍቶ ተናግሮአል። ቅዱስ ያሬድ ይህን ሲናገር *‹‹ዘተነግረ በኦሪት ወተሰብከ በነቢያት ወተዐውቀ በሐዋርያት ... በኦሪት የተነገረ በነቢያት የተሰበከ በሐዋርያት ታወቀ››* ብሏል። እርስዎም በተጨማሪ ሌሎች መጻሕፍትን በማገላበጥ በበለጠ ለመረዳት ይሞክሩ። ከዚህ በታች በዝርዝር የተገለጡትን በጥሞና በመከታተል እርስዎ ከተረዱት ጋር ያገናዘቡ።

- *‹‹እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር››* ዘፍ፡-1፡26 ‹እግዚአብሔርም አለ› ሲል አንድነቱን፤ ‹ሰውን በመከልካችን እንደ ምሳሌአችን› ሲል ሦስትነቱን
- *‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለምና፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት...››* ዘፍ፡-2፥18-19 ‹እግዚአብሔር አምላክ አለ› ሲል አንድነቱን፤ ‹የምትመቸውን ረዳት እንፍጠርለት› ሲል ሦስትነቱን

ውድ ተማሪያችን እዚህ ጋር ‹እግዚአብሔር አለ› ሲል አንድነቱን፤ ‹እንፍጠር› ሲል ከአንድ በላይ መሆኑን ግልጽ ያደርገዋል። አንዳንድ ሰዎች እንፍጠር የሚለው መላእክትን ነው ይላሉ፤ ከዚህ በፊት እንዳየነው እግዚአብሔር በባሕርይው ሁሉን አድራጊ፣ ምንም የሚሳነው ነገር የለም። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይላል፡-

- *‹‹ከማኅፀን የሠራህ፣ የሚቤዠህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ሁሉን የፈጠርሁ፣ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ፣ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ከእኔ ጋር ማን ነበረ?››* ኢሳ፡-44፥24 ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው እግዚአብሔር ሲፈጥር የማንም ርዳታ እንዳላስፈለገው ነው።
- *‹‹እግዚአብሔርም አለ፡- እነሆ አዳም መልካምና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ››* ዘፍ፡-3፣22
- *‹‹ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ቃል እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው››* ዘፍ፡-11፤1-9 በእነዚህ ጥቅሶች ላይ ተናጋሪው አንድ ሲሆን ሌሎች የሚሰሙ አካላት መኖራቸው ከሁለት በላይ መሆኑን ግልጽ ያደርግልናል።
- *‹‹በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔርም በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት። ዓይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ፤ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ ወደ ምድርም ሰገደ››* ዘፍ፡-18፤1-2 ውድ ተማሪያችን በዚህ ጥቅስ በትክክል እግዚአብሔር ለአብርሃም በሦስት አካላት መልክ እንደተገለጸለት እናያለን። አብርሃምም በአንድነትም በሦስትነትም ሲናገር እናያለን።
- *‹‹የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላቸ፤ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ››* መዝ፡-32፥5-6
    - ‹የእግዚአብሔር ቸርነት› ሲል አብን
    - ‹በእግዚአብሔር ቃል ሲል› ወልድን
    - ‹በአፉ እስትንፋስ› ሲል መንፈስ ቅዱስን ገልጿል
- ነቢዩ ኢሳይያስም በተመሳሳይ መልኩ ሲናገር *‹‹አንዱ ለአንዱ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለችና እያሉ ይጮኻሉ››* ኢሳ፡-6፥2-6
    - ‹ቅዱስ›- ማለታቸው አንድነታቸውን
    - ሦስት ጊዜ መደጋገማቸው ሦስትነቱን ይገልጣል

- *‹‹...ኢየሱስም ከተጠመቀ በኃላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በራሱ ላይ ሲመጣ አየ። እነሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ፣ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ እርሱ ነው አለ››* ማቴ፡-3፡13-17

  ጌታችን በዮርዳኖስ ሲጠመቅ አብ በሰማይ መሰከረ፤ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወረደ። አባቶች ምሥጢረ ሥላሴ በግልጽ የታወቀው የተገለጠው በዮርዳኖስ ነው ብለዋል። መንፈስ ቅዱስ ለምን በርግብ አምሳል ወረደ ቢሉ፤ ርግብ የዋህ ናት መንፈስ ቅዱስም ኃዳጌ በቀል ይቅር ባይ ነውና። መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መውረዱ ርግብ ቢመቷት እንቁላሏን ቢያፈርጡባት ፈጽመው ቤቷን ካለፈረሱባት በስተቀር ቤትዋን ትታ እንደማትሔድ መንፈስ ቅዱስም ኃጢአት ቢሠሩ ቢበድሉ ፈጽመው ካልካዱት በቀር ከሰው አይለይም።
- *“የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን”* 2 ቆሮ፡-13፣14 ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ሲባርካቸው ይህን በኦሪት ነቢዩን ሙሴን እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲህ ብለህ ባረካቸው ብሎ የተናገረውን ነው፡-

  *“እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ ሰላምንም ይስጥህ”* ዘኍC፡-6፣24 *‹‹በመጀመሪያው ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ››* ዮሐ፡-1፣1

  *“ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመስክራል››* ዮሐ፡-15፣26

ውድ ተማሪያችን ሰዎች ክብር ይግባውና ‹መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ያንሣል፤ ተላኪ ነው› የሚሉ አሉ። ይህ ግን ስህተት ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ብሎ ይናገራል፡-

*‹‹ታዳጊህ የእስራኤል ቅዱስ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ፣ በምትሔደበትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ። ትእዛዜን ብትሰማ ኖሮ ሰላምህ እንደ ወንዝ ጽድቅህም እንደ ባሕር ሞገድ በሆነ ነበር፤ ዘርህም እንደ አሸዋ የሆድህም ትውልድ እንደ ምድር ትቢያ በሆነ ነበር›› ኢሳ፡-48፣17*

እግዚአብሔር የሚለንን ነገር መስማት እንዳለብን ማወቅ አለብን *‹‹እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርሁም፤ ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነብርሁ፣ አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል››* ኢሳ፡-48፣16 በማለት መንፈስ ቅዱስም እንደሚልክ ይናገራል። እዚህ ላይ ሥላሴ በፈቃድ በመላክ አንድ መሆናቸው መበላለጥ እንደሌለባቸው ያሳውቃል።

*‹‹አየሁም እነሆም በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር፤ ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም የመንፈስ ቅዱስም ስም በግምባራቸው የተጻፈባቸው መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ›› ራእ፡-14፡1*

*‹‹እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እያመጠመቃችኋቸው ያዘዛችኋችሁንም ሁሉ እንዲጠበቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው››* ማቴ፡-28 ፣19



# መልመጃ ሁለት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ ስጡ**

1) የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት በምን በምን እንደሆነ በዝርዝር ይግለጹ?

   _____

   _____

2) የሥላሴ አካል *ምሉዕና ረቂቅ* ነው፤ ምሉዕነታቸውና ረቂቅነታቸው እንዴት እንደሆነ አብራሩ?

   _____

   _____

3) በኦሪት ዘፍጥረት ላይ *‹‹እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር››* ዘፍ 1÷26 ይህ ጥቅስ የሚገልጸውን ትርጉም በዝርዝር አስረዱ?

   _____

   _____

# ምዕራፍ ሦስት
# ምሥጢረ ሥጋዌ



## መግቢያ

ውድ ተማሪያችን! እንኳን ወደ ሦስተኛው ምዕራፍ በሰላም መጡ! በዚህ ምዕራፍ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ወይም ስለ አምላክ ሰው መሆን፣ ስለተዋሕዶ፣ በአጠቃላይ ከሦስቱ አካላት ስለ እግዚአብሔር ወልድ የሰውን *ሥጋ* መዋሐድና ሰውን ስለማዳን ያለው የቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ ቀርቦልዎታል።

### ዓላማዎች

ይህን ምዕራፉ በሚገባ አጥንተው ከጨረሱ በኋላ:-

- የምሥጢረ *ሥጋዌን* ትርጉም ያብራራሉ፤ እንዲሁም
- የእግዚአብሔር ወልድን ሁለት ልደታት ገልጸው ያስረዳሉ፤
- ነገረ ማርያም ምን እንደሆነና ነገረ ማርያም ለምሥጢረ *ሥጋዌ* ያለውን ድርሻ ያብራራሉ፤ በተጨማሪም
- አምላክ ሰው የሆነበትን ምክንያት ይገልጻሉ

## 3.1 ሥጋዌ ማለት ምን ማለት ነው?

*ሥጋዌ* ‹‹ተሠገወ›› - ‹*ሥጋ* ሆነ፣ *ሥጋን* ለበሠ፣ ኅላ፣ ገዘፈ› ከሚል የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ *ሥጋን* መዋሐድ፣ ሰው መሆን ማለት ነው። ምሥጠረ *ሥጋዌ* ማለት ደግም ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ሰው የሆነበት የሰውን *ሥጋ* የተዋሐደበት ምሥጢር ነው። ዮሐንስ በወንጌሉ *‹‹ቃል ሥጋ ሆነ … በእኛም አደረ››* ዮሐ፡-1፣14 በማለት እንደተናገረ።

ውድ ተማሪያችን እዚህ *ጋር* መረዳት የሚኖርብን እግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት እንዳሉት ነው። ይህንንም ከዚህ በታች እንመለከታለን።

## 3.2 የእግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት

እግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት አሉት፤ እነርሱም ቅድመ ዓለም ከአብ፣ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ነው።

#### ሀ. ቅድመ ዓለም

ዓለማት ከመፈጠራቸው፣ ብርሃናት ከመዘርጋታቸው በፊት ከአብ ያለ እናት ተወለደ። ይህ ማለት ቀደም ብለን በምሥጢረ ሥላሴ ላይ እንዳየነው አብ ወልድን ቢወልድ መንፈስ ቅድስን ቢያሠርጽ ከእነርሱ አስቀድሞ ነበር አይባልም። እንደሰው ሰውኛ አይደለም። ለእኛ መገኘት የእናትና የአባቶቻችን ቅድመና ያስፈልጋል፤ በሥላሴ ዘንድ እንዲህ አይደለም

አብ ከወልድ ወልድ ከመንፈስ ቅድስ ለዓይን ጥቅሻ ያህል ተለያይተው አያውቁም። ዮሐንስ በወንጌሉ ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *‹‹እኔን ያየ አብን አይቶአል›› ‹‹እኔና አብ አንድ ነን››* በማለት የተናገረውን እንደጻፈ። ዮሐ፡-14፥8-11፤ ዮሐ፡-10፥ 30። ወንጌላዊው ማቴዎስም እግዚአብሔር ወልድ (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ከአብ እንደተወለደ ሲጽፍልን እንዲህ ብሎአል። -

*‹‹እነሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ ይህ ነው አለ››* ማቴ፡-3፣17 *"...መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል››* ሉቃ፡-1፣35 *‹‹እግዚአብሔር አለኝ፡- አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ››* መዝ፡-2፣7 *‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዶአልና››* ዮሐ፡-3፣16 ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች የሚገልጹልን እግዚአብሔር ወልድ ቅድመ ዓለም ከአብ እንደተወለደና የአብ አንድያ ልጁ እንደሆነ እንደገና ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም እንደተወለደ ነው።

### ለ. ድኅረ ዓለም

እግዚአብሔር አምላክ አዳም በበደለ ሰዓት ለአዳም ቃል ኪዳን ሲገባለት ከአምስት ቀን ተኩል /ከ5500 ዘመን/ በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ሲል ቃል ገባለት። ሰዓቱ በደረሰ ጊዜ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ግብር በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና ተወልዷል። ይኸን ነው ሁለተኛ ልደት ወይም ድኅረ ዓለም፤ ዓለም ከተፈጠረ፣ ጊዜ ከተቆጠረ፣ ቀላያት ከተዘረጉ በኋላ የእግዚአብሔር ወልድ ሁለተኛ ልደት የምንለው።

*‹‹ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፡- እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች››* በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችንን እንደምትወልደው ተናግሮአል። ኢሳ፡-7፥14

*‹‹ሕፃን ተወልዶልናልና፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት፤ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል››* ኢሳ፡-9፥6

*‹‹በነቢይ ከጌታ ዘንድ፡- እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፤ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው››* ማቴ፤-1፥23

*‹‹በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፤ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ››* ሉቃ፡-1÷26

*‹‹መልአኩም እንዲህ አላት፡- ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ፤ እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ፣ እርሱም ታላቅ ነው፤ የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ...››* ሉቃ፡-1÷30-32 ከላይ የተመለከትናቸው ጥቅሶች ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ወልድን በመንፈስ

ቅዱስ ግብር በድንግልና እንደወለደችው የሚያስረዳን ነው። ከእርስዋ የተወለደው የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ለሕዝብ ሁሉ መድኃኒት እንደሚሆን ተናግሮአል። ኢሳይያስ እንዳለው። ኢሳ፡-9÷6።

ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው እግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት እንዳሉት ተመልክተናል። ይኸውም ቅድመ ዓለም ያልነው ከአብ ያለ እናት በዚህ ጊዜ ሳይባል እራሱ እግዚአብሔር በሚያውቀው ጥበብ ፍጥረታት በማያውቁት ምሥጢር ከአብ ተወለደ፤ ሁለተኛው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ *ሥጋ፣* ከነፍሷ ነፍስ፣ ከደሟ ደም በመንሣት በድንግልና ተፀንሶ፣ በድንግልና ተወልዷል። ይህ ዘመናት ከተቆጠሩ በኋላ ያለው ልደት ነው። እንግዲህ ከላይ ጀምረን እንደተመለከትነው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በትንቢት ጌታችንን እንደምትወልደው እንደተነገረ ይህም በሐዲስ ኪዳን እንደተፈጸመ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም እመ አምላክ (የአምላክ እናት) እንደምትባል አይተናል። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን እንዴት ልትወልደው ቻለች? ሰማይና ምድር የማይችሉትን አምላክ እንዴት ቻለች? አባቶች ሲናገሩ ውኃን ከጥሩ ነገርን ከስሩ ይላሉ፤ እኛም ስለ አምላክ ሰው መሆን ከማንሣታችን በፊት አምላክ ለመረጣት ሰው እንዲሆን ለፈቀደባት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተወሰነ ማንሣት ተገቢ ነውና። ኢሳይያስ በትንቢቱ እንዲህ እንዳለ፡- *‹‹የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር››* እንዳለ። ኢሳ፡-1፥9 ንጹሕ ዘር የተባለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ባትቀርልን፤ አምላክን ባትወልድልን ኑሮ ጠፍተን በቀረን ነበርና። እርስዎም ሌሎች መጻሕፍትን በማየት መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ይረዱ።

## 3.3 ነገረ ማርያም

የእመቤታችን ቅድመ አያቶቿ በምግባር በሃይማኖት ጸንተው ይኖሩ የነበሩ ቴክታና ጸጥሪቃ ይባላሉ ይህ ቀራችሁ የማይባሉ ባለጸጎች ነበሩ፤ የሀብታቸውም ብዛት ይህን ያህላል የማይባል ነበር።

እነዚህ ባለጸጎች ግን ይህንን ያህል ሀብት ንብረት ቢኖራቸውም በሕይወት እያሉ ስማቸው የሚጠራበት ቢሞቱ ንብረታቸውን የሚያወርሱት ልጅ አልነበራቸውም ከዕለታት አንድ ቀን ጸጥሪቃ ወደ ቤተ መዛግባቱ ገብቶ ያለውን ሀብት ንብረት ቢመለከት አዘነ ሚስቱም ስለሞን ታዝናለህ ብትለው፡- *‹እኔ መካን አንቺ መካን ይህ ሁሉ ገንዘብ ለማን ይሆናል?›* አላት። *‹እግዚአብሔር ከእኔ ልጅ ባይሰጥህ ሌላ አግብተህ ትወልድ ዘንድ ፈቅጄልሃለሁ›* አለችው። *‹ይህን እንዳላደርግ የእስራኤል አምላክ ያወቃል›* አላት፤ እንደዚህ እያዘኑ ሲኖሩ ራእይ አይተዋል። ይኸውም ነጭ እንቦሳ ከአብራካቸው ስትወጣ፤ እንቦሳይቱ እንቦሳን ስትወልድ እስከ ሰባት ሲዋለዱ ሰባተኛዪቱ ጨረቃን፤ ጨረቃ ደግም ፀሐይን ስትወልድ አዩ። በሀገራቸው መፈክረ ህልም /ህልም ፈቺ/ አለ፤ ቢነግሩት *‹ሰባት ደጋግ ሴቶች ልጆች ከእናንተ ዘር ይወለዳሉ ሰባተኛይቱ ጨረቃን መውለዷ ከፍጡራን በላይ የሆነች ደግ ሴት ነች፤ የፀሐይ ነገር ግን አልተገለጠልኝም ጊዜ ይፍታው›* አላቸው። ከዚያም ወደ ቤታቸው ተመለሱ፤ ቴክታም ፀነሰች ወለደችም ስሟንም **ሄኤሜን** ብላ ጠራቻት ትርጉሙ *‹እግዚአብሔር ስዕለታችንን ሰማን› ማለት ነው።* ሄኤሜንም ለአቅመ ሔዋን ስትዳርስ አጋቢት እርስዋም ሴት ልጅ ወለደች ስሟን **ደርዲ** አለቻት፤ *‹ከአባቶቻችን ወገን የተወለደች› ማለት ነው።* ደርዲም በሥርዓት ካደገች በኋላ አጋቢት እርስዋም ሴት ልጅ ወለደች ስሟን **ቶና** አሏት፤ ትርጉሙ *‹ራእይ አይተን የወለድናት› ማለት ነው፤* ቶናህም **ሲካርን** ትወልዳለች፤ ሲካር ማለት *‹ከዘመዶቻችን ወገን የተወለደች› ማለት ነው፤* ሲካርም **ሴትናን** ትወልዳለች፤ ሴትና ማለት *‹ሙያዋ ያማረ› ማለት ነው፣* ሴትናም **ሔርሜላን** ትወልዳለች፤ ሔርሜላ ማለት *‹ከባለጸጎች ወገን የተወለደች› ማለት ነው፣* ሔርሜላም በሥርዓት ካደገች በኃላ አጋቢት፤ እርስዋም **ሐናን** ወለደ፤ ሐና ማለት *‹በሃይማኖት በምግባር የጸናች፣ ስጦታ /ጸጋ/› ማለት ነው።*

ሐናን በሥርዓት ካሳደጓት በኋላ ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ ከይሁዳ ወገን ከሆነ አያቄም ለሚባል ሰው አጋቧት፤ ሐናና ኢያቄም በደስታ ሲኖሩ ከአያቶቻቸው የነበረው መካንነት በእነርሱም ደረሰ። ልጅን ሳይወልዱ ለብዙ ዘመናት ቆዩ፤ በጸምና በጸሎት እግዚአብሔርን ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ ይለምኑት ነበር፤ ሐናም ከጎረቤቶቿ የሚደርስባት ነውርና ስድብን የሚያርቅላት አንድ ልጅ ይሰጣት ዘንድ በመለመን አዘነች።

በሌላ ወቅትም ቤተመቅደስ መሥዋዕት እናቅርብ ብለው ቢሔዱ ሊቀ ካህናቱ ሮቤል *‹የመካኖቹን መሥዋዕት አትቀበል›* ይላል እናንተም *‹‹ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏዋት› ያለውን የአዳምን ቃል ኪዳን ያስቀረባቸሁ አይደለችሁምን? እግዚአብሔር ቢጠላችሁ እንጂ ቢወድዳችሁ ልጅ በሰጣችሁ ፣ መሥዋዕትንም ለማቅረብ ዕድል ባገኛችሁ ነበር›* ብሎ መለሰላቸው። እንደዚሁም አረጋውያን ከሆኑ እስራኤል የወለዱ ሰዎች የሚመገቡትን ተረፈ መሥዋዕትም ከለከላቸው፤ እያዘኑ ሲመለሱ ከዛፍ ሥር ተቀምጠው ርግቦች ከልጆቻቸው ሲጫወቱ ዕጸዋትም አበብው አፍርተው አይተው ርግቦችን በባሕርያቸው እንዲራቡ ዕጽዋትን እንዲያብቡ እንዲያፈሩ የምታደርግ የእኔ ተፈጥሮዬ ከድንጋይ ይሆን ልጅ የነሳኸኝ ከልብ አዘነች፤ ምርር ብላም አለቀሰች ከዚያም ሐናና አያቄም እግዚአብሔር የለመኑትን የማይነሳ የነገሩትን የማይረሳ መሆኑን ተረድተው ብጽዓት /ስዕለት/ ገቡ፤ ‹ወንድ ልጅ ብንወልድ ወጥቶ ወርዶ አርሶ ቆፍሮ ይረዳን አንልም ለቤተ እግዚአብሔር አንጣፊ ጋራጅ ይሆናል፤ ሴት ብንወለድ እንጨት ሰብራ ውኃ ቀድታ ትርዳን አንልም ለቤተ እግዚአብሔር መሶበ ወርቅ ሰርታ መጋረጃ ሰፍታ ትኑር› በማለት ለመኑ።

ከዚያም በኋላ ሐምሌ 30 (ሠላሳ) ድንቅ ሕልም ተመለከቱ፤ ነሐሴ 7 (ሰባት) በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ሱባዔ ከያዙ በኋላ እመቤታችን ተፀነሰች። ሐናም እመቤታችንን በመልአኩ ብሥራት በፈቃደ እግዚአብሔር በፀነሰች ጊዜ ብዙ ተአምራትን አድርጋለች፤ ከዘመዶቿ ወገን የምትሆን አንድ ዓይኗ ማየት የማትችል ቤርሳቤህ የምትባል ነበረች ሐናን ለመጎብኘት በመጣች ጊዜ *‹ሐና እግዚአብሔር በረድኤት ጎበኘሽ መሰለኝ›* ብላ ማሕፀኗን ዳስሳ ዓይንዋን ብትነካው በርቶላታል፤ ሌላው ሳሚናስ የሚባል የአጎቷ ልጅ ሲሞት ሐና የአልጋውን ሽንኮር እየዘረች ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት ተነሥቶ *‹የጨረቃ እናቷ የፀሐይ አያቱ›* በማለት ሕልም ፈቺው ያልፈታውን ተርጉሞ ተመልሶ ዐርፎአል። ቀናተኞች አይሁድ ይህ ገና ሳይወለድ በእናቱ ማሕፀን እንዲህ ያደረገ ከተወለደማ እንዴት ያደርገን? ቀድሞ ከእነዚህ ወገን ዳዊትና ሰሎሞን አርባ አርባ ዘመን ገዙን፤ አሁን ደግሞ ሐናና ኢያቄም በእኛ ላይ ሊነግሡ አይደለምን በማለት ኑ በድንጋይ ወግረን በእሳት አቃጥለን እናጥፋቸው ብለው በጠላትነት ተነሡባቸው። መልአኩም ወደ ሊባኖስ ተራራ እንዲወጡ አዘዛቸው በዚያም ግንቦት አንድ ቀን በሊባኖስ ተራራ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደች። እመቤታችን በተወለደች ጊዜ ሊባኖስ ተራራ አበራ፤ የአዳም ተስፋው ተፈጽሟል። እዚያ ከቆዩ በኋላ ስሟን ማርያም ብለው አወጡላት።

### 3.3.1 የእመቤታችን የስሟ ትርጓሜ

- **ማርያም፡-** የሚለው የእመቤታችን ስም ብዙ ትርጓሜዎችን የያዘ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የተወሰኑትን እንመለከታለን።

- **ማርያም**፡- ማለት *‹መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት› ማለት ነው*። በዚህ ዓለም ያለ ዓይነ ስውር የሆነ ሰው መሪ በትር እንደሚያስፈልገው ሁሉ ወደ ሰማያዊው ዓለም ለሚጓዙ ሁሉ መሪ የሆነችና በታመነው አማላጅነቷ መርታ መንግሥተ ሰማያት የምታስገባ፣ ሥርየተ ኃጢአትን፣ በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስን ከልጅዋ ከወዳጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ እየለመነችና እያማለደች የምታሰጥ ማለት ነው። መዝ፡-44፣9-12

- **ማርያም፡-** ማለት ‹*ፍጽምት*› ማለት ነው ለጊዜው መልክን ከደም ግባት *ጋር* አስተባብራ ይዛ ተገኝታለችና። ፍጻሜው ግን ንጽሐ *ሥጋ* ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡናን አንድ አድርጋ አስተባብራ ይዛ ተገኝታለችና። ፍጽምት ትባላለች። መኃ. መኃ. ዘሰ፡-4፤7፣ ሉቃ፡-1፤28-42

- **ማርያም፡**- ማለት *‹ጸጋ ወሀብት›* ማለት ነው። ለጊዜው ለእናትዋ ለቅድስት ሐና እና ለአባትዋ ለቅዱስ ኢያቄም ጸጋና ሀብት የስእለት ልጅ ሆና ከፈጣሪዋ ዘንድ ተሰጥታለች። ፍጻሜው ግን በዕለተ ዓርብ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ላይ ሳለ የጌታ ወዳጅ በሆነው በወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ አማካኝነት ለዓለም ሁሉ እናት ሆና ከፈጣሪዋ ከልጅዋ ከወዳጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ በአደራ ቃል በቀራንዮ መስቀል ስር ተሰጥታለችና። መዝ፡-86፤5 ፣ ዮሐ፡-19፤25-27

- **ማርያም፡-** እመቤታችን በዕብራይስጥ ቋንቋ ‹*ማሪሃም*› ትባላለች። ‹*ማሪ*› ማለት እመቤት ማለት ነው፤ ‹*ሃም*› ማለት ደግሞ ብዙኃን ማለት ነው። በዕብራይስጥ ማሪሃም ማለት የብዙሐን እመቤት ማለት ነው። የዓለም ሁሉ እመቤት የሆነች የእናት አማላጅ ናትና።

- **ማርያም** የሚለውን የስሙን ፊደላት ትርጉም ስንመለከት ደግሞ፡-
  - **ማ፡-** *ማኅደረ መለኮት /የመለኮት ማደሪያ/* ማለት ነው። ዘጸ፡-3፤2፣ መዝ፡-45፤4፣መዝ፡-131፤13-14
  - **ር፡-** *ርግብየ ይቤላ* ሰሎሞን /ሰሎሞን ርግቤ ያላት/፣ በጥፋት ውኃ ጊዜ ለኖኅ ቅጽለ ዘይት /የለመለመ የወይራ ቅጠል/ በአፍዋ ይዛ የጥፋት ውኃ መጉደሉን ያበሠረች ለምሕረት የመጣች ርግብ ማለት ነው። (መኃ. መኃ. ዘሰ፡-5፣2፤ ዘፍ፡-8፤8)
  - **ያ፡-** *ያንቃዕዱ ኀቤኪ ከርሉ ፍጥረት /*ከአንቺ አማላጅነት ያመኑ ሁሉ ቅድስት ሆይ ለምኝልን እያሉ ወደ አንቺ ይለምናሉ/ ማለት ነው። መዝ፡-44፣12
  - **ም፡-** *ምስአል ወምስጋድ ወምስተሥራየ ኃጢአት /*ኃጢአትን ለማስተሥረይ ምሕረትን ከፈጣሪ እያማለድሽ የምታሰጪ ማለት ነው/ ዮሐ፡-2፣3

ወድ ተማሪያችን ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስለ ስምዋ ትርጓሜ በተወሰነ መልኩ እንደተገነዘቡ እናምናለን እርስዎም መጻሕፍትን በማገላበጥ የበለጠ እውቀት ያዳብሩ። ከዚህም በመቀጠል ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በብሉይ ኪዳን የተመሰለችበትን ምሳሌ እንመለከታለን።

### 3.3.2 እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በምሳሌ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በብዙ ኅብርና ምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስና በአበው ስትመሰል ኖራለች። አባታችን አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ላይ፡- *‹ምስጋናን የተመለሽ ድንግል ሆይ በማንና በምን ምሳሌ እንመስልሻለን?›* እያለ ከአዳም አንሥቶ በብዙ ምሳሌ ይመስላታል፤ ይህ ሁሉ ግን እመቤታችንን ለመግለጽ የማበይቃ መሆኑን እናውቃለን። ለምን ቢባል ሰማይና ምድር የማይችሉትን አምላክ እመቤታችን በማሕፀንዋ ተሸክመዋለችና። ለትምህርታችን ይረዳን ዘንድ ለእመቤታችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት የተወሰኑትን ምሳሌያትዋን እንመለከታለን።

### ሀ. የመጀመሪያቱ ምድር (የማክሰኞ ዕለት እርሻ)

እግዚአብሔር አምላክ ፍጥረታትን ሲፈጥር በማክሰኞ ዕለት አዝርዕትን፣ አትክልትን፣ ዕጸዋትን ፈጥሮአል። እነዚህ ሁሉ ግን የተገኙት ዘር ሳይጣልባት፣ ገበሬ ሳይግርባት ያለ ዘር ነው። የመጀመሪያዪቱ ምድር (የማክሰኞ እርሻ) ዘፍ፡-1÷12 እነዚህን ሁሉ አስገኝታች። የማክሰኞ ዕለት ምድር ምንም አልነበረበትም ባዶዋን ነበረችና። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ያለወንድ ዘር በድንግልና ፀንሳ በድንግልናም ወልዳለች፤ የማክሰኞ ዕለት እርሻ ዘር እንዳልተጣለበት እመቤታችንም በመልአኩ ብሥራት ያለወንድ ዘር ጌታችንን አስገኝታለች።

የማክሰኞ ዕለት እርሻ ምግበ *ሥጋ* የሆነውን አስገኝታለች። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን ምግበ *ሥጋ* ምግበ ነፍስ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወልዳልናለች፤ የማክሰኞ ዕለት እርሻ ከዚያ በኋላ ብዙ ጊዜ ታርሳለች ዕጸዋትንም አስገኝታለች፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን ጌታችን ስትፀንስ ድንግል፣ ከመፀነስዋ በፊት ድንግል፣ ከወለደችም በኋላ ድንግል ናት። አንድያ ልጇ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። *‹‹በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች››* መዝ፡-44÷9 *‹‹ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው ነውርም የለብሽም››* መኃ. መኃ. ዘሰ፡-4÷7

*‹‹ወደ ምሥራቅ ወደሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም፡- ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና፤ ተዘግቶ ይኖራል››* ሕዝ፡-44÷1 በማለት ቅዱስ ዳዊት ልጁ ሰሎሞንና ነቢዩ ሕዝቅኤል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከመውለዷ በፊት በወለደች ጊዜ ከወለደችም በኋላም ድንግል መሆኗን ተናግረዋል።

### ለ. የኖኅ መርከብ

እግዚአብሔር ኖኅን ከጥፋት ውኃ እንዲድን መርከብን እንዲሠራ አዝዞት ነበር፤ ሦስት ክፍል ያላት መርከብ ሠርቶ ኖኅና ቤተሰቦቹ ከጥፋት ውኃ ድነዋል። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም የኖኅ መርከብ ትባላለች፣ የኖኅ ቤተሰቦች ከጥፋት የዳኑት በመርከብዋ ውስጥ ገብተው ነው፤ እኛም ከጥፋት ከገሃነም እሳት ለመዳን በእመቤታችን አማላጅነት መተማመን ወደ እርስዋ መጠጋት ያስፈልገናል። ኢሳ፡-1÷9፤ ዘፍ፡-7÷2-23

### ሐ. የያዕቆብ መሰላል

ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው ተጣልቶ ሲሔድ ደክሞት ተኛ በሕልሙ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ተዘርግቶ መላዕክት ሲወጡበት ሲወርዱበት ተመለከተ፤ በመሰላሉ ላይ እግዚአብሔር ተቀምጦበት ነበር። ያዕቆብም ከሕልሙ ነቃ፤ ያንን ቦታ ቤቴል ብሎ ጠራው የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው፤ እመቤታችን የያዕቆብ መሰላል ትባላለች። መሰላሏ ከምድር እስከ ሰማይ ደርሶ ነበር በእመቤታችን አማካኝነት ምድራውያን ሰዎች ከሰማውያን መላእክት ጋር ታርቀዋልና። በመሰላሉም መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ነበር - እመቤታችንም ጌታችን በወለደችው ጊዜ ለምስጋና ለብሥራት መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ነበር። ሉቃ፡-2÷6-20፤ ዘፍ፡-28÷10-22

### መ. የጌዴዎን ጸምር

*‹‹ጌዴዎንም እግዚአብሔርን፡- እንደተናገርህ የእስራኤልን ልጆች በእኔ እጅ ታድን እንደሆነ እነሆ በአውድማው ላይ የተባዘተ የበግ ጠጉር አኖራለሁ፤ በጠጉሩ ላይ ብቻ ጠል ቢሆን በምድሩም ላይ ደረቅ ቢሆን እንደተናገርህ የእስራኤልን ልጆች በእኔ እጅ እንድታድናቸው አውቃለሁ አለ። እንዲሁም ሆነ፤ በነጋው ማልዶ ተነሣ፤ ጠጉሩንም ጨመቀው፤ ከጠጉሩም የተጨመቀው ጠል ቆሬ ሙሉ ውኃ ሆነ። ጌዴዎንም እግዚአብሔርን፡- እኔ ይህን አንድ ጊዜ ስናገር አትቆጣኝ፤ እኔ ይህን አንድ ጊዜ በጠጉሩ እባክህ ልፈትን አሁንም በጠጉሩ ብቻ ላይ ደረቅ ይሁን፤ በምድሩም ላይ ጠል ይሁን አለው። እግዚአብሔርም በዚያ ሌሊት እንዲሁ አደረገ፤ በጠጉሩ ብቻ ላይ ደረቅ ሆነ፤ በምድሩም ላይ ጠል ሆነ››* መሳ፡-6፣36-40 እመቤታችን በጌዴዎን ጸምር መመሰሏ ጤሉ ጸጉሩን ብቻ መንካቱ ሌላው ምድር ደረቅ መሆኑ ከሌሎች ሴቶች (ከፍጥረታት) ሁሉ ለይቶ በእመቤታችን ማደሩን፤ ሌሎች ሴቶች ግን አምላክን ለመውለድ አለመመረጣቸውን ያስረዳል፤ ሌላው ምድር ጤሉ ወርዶበት ጸጉሩን አለመንካቱ ኃጢአት በሰው ዘር ሁሉ ላይ ሲነግሥ እመቤታችን ግን የአዳም ውርስ ኃጢአት እንዳልነካት እርስዋን ለይቶ እንዳስቀመጣት የሚያስረዳ ነው። ኢሳ፡-1÷9 በሉቃስ ወንጌል ላይ እንደምናነብበው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን እንዳበሠራት በመንፈስ ቅዱስ ግብር ያለ ወንድ ዘር በድንግልና አምላክን ወልዳዋለች።

### 3.3.3 እመቤታችን ጌታችንን እንደምትወልድ በትንቢት

ውድ ተማሪያችን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትወልደው ቀደም ብሎ በነቢያት የተነገረ ነው እንጂ እንዲሁ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ የሆነ አይደለም። በተአምረ ማርያም መግቢያ ላይ እንደምናየው እመቤታችን አስቀድማ በአምላክ ሕሊና ታስባ ትኖር እንደ ነበር። ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ ሲናገር *‹‹የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኑሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ጎሞራ በመሰልን ነበር››* አለ ኢሳ፡-1÷9

ዘር የተባለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ጌታችንን እንደምትወልደው አብልጠውና አስፍተው ከተናገሩት ቅዱስ ዳዊት እና ነቢዩ ኢሳይያስን እንመለከታለን

*‹‹ልጄ ሆይ ስሚ እደ ጆሮሽንም አዘንብዪ ወገንሽን የአባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወድዶአልና እርሱ ጌታሽ ነውና››* መዝ፡-44÷10-11 ቅዱስ ዳዊት እመቤታችን ከእርሱ ዘር እንደምትወለድ አውቆ ልጄ አላት፤ ንጉሥ ፈጣሪሽ እግዚአብሔር ንጽሕናሽን ቅድስናሽን አይቶአልና አለ፤ ይህንን አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ላይ ሲናገር፡-

> ‹‹እግዚአብሔር በሰማይ ሆኖ ምሥራቅና ምዕራብን ሰሜንና ደቡብን ተመለከተ፤ አሻተተ እንዳንቺ ያለ አላገኘም... ደም ግባትሽንም ወደደ፤ የሚወድደውን አንድያ ልጁን ወደ አንቺ ሰደደ›› ፤ ‹‹ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው እርሱም እናቱን ፈጠረ›› እንዳለ ቅዱስ ቄርሎስ

*‹‹ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፤ በውስጧም ሰው ተወለደ እርሱም ልዑል መሠረታት››* መዝ፡-86÷5 ፍጥረታት ሁሉ እመቤታችን፣ እናታችን፣ አማላጃችን ቅድስት ድንግል ማርያም ይላል ከእርስዋ የዘለዓለም አምላክ ሰው ሆኖአልና፤ እርሱ ራሱ የፈጠራት እናት እንድትሆነው ነው። ሉቃ2÷48 *‹‹ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል››* ብላ እንደተናገረች።

*‹‹እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና፤ ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና እንዲህ ብሎ፡- ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ››* መዝ፡-131÷13-14 እመቤታችን እግዚአብሔር አምላክ ከማንም በላይ እንደመረጣት እናቱም እንደምትሆን ለዘለዓለምም ማደሪያው እንደሆነች ተናግሯል።
*‹‹በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝ ትቆማለች››* መዝ፡-44÷9 የወርቅ ልብስ የሚለው ንጽሕናውን፣ ድንግልናዋን ነው።

## ***ኢሳይያስ ሲናገር***

*‹‹ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች››* ኢሳ፡-7÷14 በማለት እመቤታችን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንደምትወልድ ተናግሮአል። ይህም በእመቤታችን መፈጸሙን ማቴዎስ ሲያስረዳን፡- *‹‹ጌታ በነቢይ ዘንድ፡- እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፤ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው››* ማቴ፤-1፥23 የተነገረው ትንቢት በእመቤታችን መፈጸሙን ይነገራል።

*‹‹ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና ዓለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል››* ኢሳ፡-9÷6 በሉቃስ ወንጌል ላይ እንደምናነብበው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን እንዳበሠራት በመንፈስ ቅዱስ ግብር ያለወንድ ዘር በድንግልና እንደምትወልድ ተናግሮአል። *"በስድተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሚሆን ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፤ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ "* ሉቃ፡-1፣26 በማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንደተላከ ይናገራል።

*‹‹መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ፡- ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት››* ሉቃ፡-1÷28 እዚህ ጋር መልአኩ እመቤታችንን ከሴቶች የተለየች፣ በንጽሕና በቅድስና የጸናች መሆኗን፣ ጸጋን ሁሉ የተመላች የአምላክ እናት ለመሆን የተመረጠች መሆኗን ይገልጻል። ቅዱስ ጳውሎስ የጸጋ ሥጦታ የተለያ እንደሆነ ይናገራል *‹‹የጸጋም ሥጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው››* 1 ቆሮ፡-12÷4 በማለት ተናግሮአል። እመቤታችን ግን የጸጋ ሀብታት ሁሉ ለእርስዋ የተሰጣት ጸጋን የተመላች መሆኑን እንረዳለን።

*"መልአኩም እንዲህ አላት፡- ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለምዋልነትን አግኝተሻልና አትፍሪ እነሆ ትጸንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ እርሱም ታላቅ ነው የልዑል የእግዚአብሔር ልጅም ይባላል"* ሉቃ፡-1፣30-31 በማለት ከእርስዋ የሚወለደው የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለሕዝብ ሁሉ መድኃኒት እንደሚሆን ተናግሯል። ኢሳይያስ እንዳለው። ኢሳ፡-9÷6

መልአኩ እመቤታችንን ልጅ ትወልጃለሽ ሲላት እንዴት ይሆናል? ምድር ያለ ዘር ሴት ልጅ ያለ ወንድ እንዴት ይሆናል? ስትለው እንደሰው ልማድ አይደለም፤ ከአንቺ የሚወለደው የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ነው አላት።

*‹‹ማርያም መልአኩን፡- ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለቸው፤ መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል››* ሉቃ፡-1÷34-36

ውድ ተማሪያችን እንግዲህ ከላይ ጀምረን እንደተመለከትነው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በትንቢት ጌታችንን እንደምትወልደው እንደተነገረ ይህም በሐዲስ ኪዳን እንደተፈጸመ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም እመ አምላክ (የአምላክ እናት) ትባላለች። ውድ ተማሪያችን ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘርዝረን መጨረስ ይከብደናል በተአምረ ማርያም መጽሐፍ ላይም ሲናገር የሰማይ ሠሌዳ እንደ ብራና ቢሆን፣ የምድር ዕጸዋት ብዕር ቢሆኑ፣ ባሕር ቀለም ቢሆን፣ ስለ እመቤታችን ነገር ዘርዝረን መጨረስ አንችልም። እርስዎም ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን አባቶችን በመጠየቅ ሌሎች መጻሕፍትን በይበልጥ በማንበብ ዕውቀትዎን ያዳብሩ። የእመቤታችን ቅድስት ግንግል ማርያም ፍቅሯን በልቦናችን፣ ጣዕሟን በአንደበታችን ያሳድርብን አሜን።

## 3.4 አምላክ ለምን ሰው ሆነ?

ውድ ተማሪያችን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት እንደሆነች ሰማይና ምድር የማይችሉትን አምላክ እርስዋ በማሕፀንዋ እንደተሸከመችው አይተናል። ከዚህም በመቀጠል አምላክ ለምን ሰው ሆነ? የሰውን ሥጋ ለምን ተዋሐደ? ሰው መሆን ለምን አስፈለገው? የሚለውን በመቀጠል እንመለከታለን።

> ‹‹ኃያል ወልድን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው እስከሞትም አደረሰው››
> ቅዳሴ ማርያም

በምሥጢረ ሥጋዌ (በነገረ ድኅነት) ዋናው ምሥጢር አምላክ ለምን ሰው ሆነ? የሚለው ነው፤ አምላክ ሰው ለመሆን ክብሩን ዝቅ ያደረገው፣ እንደሰው የተራበው፣ የተጠማው፣ የተሰደደው፣ የተገረፈው፣ የተሰቀለውና የሞተው ለምንድን ነው የሚለው ነው።

ዋናው ነገር አምላክ ለምን ሰው ሆነ ሲባል መልሱ የሰው ልጆችን ለማዳን ነው ይሆናል። አባታችን አዳም *‹አትብላ›* የተባለውን ዕጸ በለስ በራሱ ፈቃድ በልቶ በርደተ መቃብር/ ፋይድ (ወደ መቃብር መውረድ/ ወደ ምድር መሰደድ) ላይ ርደተ ሲዖል (ወደ ሲዖል መውረድ) ተፈርዶበት ነበር።

- **ርደተ ፋይድ:-** ማለት ከነበረበት ቦታና ክብር ተዋርዶ ወደ ምድር መሰደድ፣ በሥጋው ተጎሳቁሎ በመከራ በችግር ላቡን አፍስሶ ጉልበቱን ከስክሶ እንዲኖር፤ ሴቲቱም ስትወልድ በችግር፣ በምጥ፣ በጭንቅ እንድትወልድ ተፈረደባቸው ማለት ነው። ዘፍ፡-3÷14-20
- **ርደተ ሲዖል፡-** ማለት በሥጋው ተጎሳቁሎ ይኖር የነበረው ሰው በነፍሱ ወደ ሲዖል ወረደ፣ በመከራ ውስጥ ሆነው በሰይጣን ግዛት ይኖሩ ዘንድ ተፈረደበት ማለት ነው።

ውድ ተማሪያችን ታዲያ አምላክ በሰማይ ሆኖ አዳምን ማዳን አይችልም ነበር? ወይም መላእክትን ልኮ ወይም በብሉይ ኪዳን ካሉት ቅዱሳን መካከል በአንዳቸው ሊያድነው አይችልም ነበርን?

_____
_____

ለምን ሰው መሆን አስፈለገው ቢባል የሚከተሉትን ምክንያቶች እናገኛለን፡-

## ሀ.ለሰው ልጆች ያለውን ፍጹም ፍቅር ለመግለጽ

እኛን የሰው ልጆችን ምንኛ እንደወደደን ለመግለጽ እኛም ፍቅሩን እንድንረዳ ሲል ነው የእኛን ባሕርይ ባሕርዩ እስከ ማድረግ ደርሶ እኛን እራሳችንን ሆኖ ሰው ሆኖ ተገልጿል።

*‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዶአልና›› ዮሐ፡-3÷16-18*

*‹‹እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም››* ዮሐ፤-15÷12-13 በማለት ለእኛ ያለውን ፍቅር ማንም ሊያደርገው የማይችል መሆኑን ጌታችን ተናግሯል። ኢሳይያስ በተመሳሳይ እኛ የሰው ልጆች ለማዳን ሲል የደረሰበትን መከራና ምንኛ እንደወደደን ሲናገር፡- *‹‹በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን››* ኢሳ፡-53÷4-5 ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን ሲያብራራው ‹‹ኃያል ወልድን ፍቅር ከሰማይ ከመንበሩ አወረደው እስከሞትም አደረሰው››

## ለ.ለአርዓያ ለአብነት

(የሰው ልጆች መሥራት ያለባቸውን ሠርቶ ለማሳየት )

እግዚአብሔር በትእዛዙ ላይ ነቀፋ የለበትም፤ የሠራቸውን ሥራዎች ትእዛዛትንም ሁሉ እርሱ ሠርቶ አሳይቶናል። የሰው ልጆች መሥራት ያለባቸውን ከኃጢአት በቀር (ኃጢአት ለባሕርይው የማይስማማው አምላክ ነውና) ሁሉንም ሠርቶ ፈጽሞ አሳይቶናል።

ለምሳሌ፡- አርባ ቀንና ሌሊት ጾሞ ጹሙ አለ፣ ጸሎትን ጸልዮ ጸልዩ ብሎ አዘዘ፣ ተጠምቆ ጥምቀታችንን ባረከልን፣ የሐዲስ ኪዳን ቁርባን ሆኖ ቅዱስ ሥጋውን እንድንበላ ክቡር ደሙን እድንጠጣ አዘዘን። ለእናቱ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ለአሳዳጊው ለዮሴፍ ይታዘዛቸው ነበር። *‹‹ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ ይታዘዝላቸውም ነበር፤ እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር››* ሉቃ፡-2÷51

*‹‹...ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ። በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ሆነ ራሱን አዋረደ፤ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ››* ሞቱም በመስቀል የሆነው ነው። ፊል፡-2÷7-11

## ሐ.ለካሳና ለቤዛ

ቀዳማዊው አዳም አትብላ የተባለውን በመብላት አምላክነትን በመመኘት ሞትን አመጣ *‹‹ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ››* ሮሜ፡-5÷12 ስለዚህ አዳም አምላክነትን በመመኘት ኃጢአት ቢያደርግ ስለሠራው በደል ምክንያት መካስ ነበረበት። አዳም (ሰው) አምላክ ሆኖ መካስ ስለማይችል፤ አምላክ ሰው ሆኖ ክሶለታል፤ ይህም ማለት አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አዳም በመገባት (በአዳም ቦታ ሆኖ) ለመካስ ሰው ሆኗል ማለት ነው።

*‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- እነሆ አዳም መልካምና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ››* ዘፍ፡-3÷22 ‹‹አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ?›› መዝ፡-21÷1 እዚህ ጋር አምላኬ አምላኬ ያለው ስለአዳም በመገባት ነው አዳም፤ በሲዖል ሆኖ እግዚአብሔር አምላኬ ለምን ተውከኝ ይል ነበርና፤ ጌታችንም በመስቀል ላይ ይህንን ቃል ደግሞታል። ማቴ፡-27÷45-47፤ ማር፡-15÷33-36 ፤ *‹‹በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ*

*በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን››* ኢሳ፡-53÷4-5

**መ. የሰይጣንን ጥበብ በመለኮታዊ ጥበቡ ለመሻር**

ሰይጣን በእባብ ተሰውሮ አዳምና ሔዋንን አስቶአቸዋል፤ ሰይጣን በጥበቡ እንዳሳተቸው ይህንን የሰይጣንን ጥበብ ለመሻር አምላክ ሰው ሆኗል።

*‹‹ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔር ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን። ከዚህችም ዓለም ገዢዎች አንዱ እንኳን ይህንን ጥበብ አላወቀውምና፤ አውቀውስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉት ነበር።››* 1 ቆሮ፡-2÷7

## 3.5 አምላክ እንዴት ሰው ሆነ?

አምላክ እንዴት ሰው ሆነ የሚለውን ከማየታችን በፊት መገንዘብ የሚገባን ነገር አለ፤ እርሱም ሁለት ዓይነት አካላት እንዳሉ ነው። እነርሱም የማይታይ፣ የማይዳሰስ አካልና የሚታይ፣ የሚዳሰስ፣ የገዘፈ አካል እንዳለ ማወቅ ይገባናል። የአምላክ (የእግዚአብሔር) አካል የማይታይ፣ ረቂቅ፣ ሊዳሰስ የማይችል፣ የራሱ የሆነ ባሕርይ ያለው አካል ነው። የሰው ልጅ አካል ደግሞ ግዙፍ የሆነ፣ የሚታይና የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ ነው። አምላክ ሰው ሆነ ስንል የማይጨበጠው በምሉዕነት ያለው፣ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው፣ አምላክ ውሱን የሆነውን የሚራበውን፣ የሚጠማውን፣ ድካም ያለበትን የሰው ልጅን አካል ነሣ፣ ተዋሐደ ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያስረዳ።

*‹‹...ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን **ከሕግም በታች** የተወለደውን ልጁን ላከ››* ገላ፡-4÷4 በማለት ተናግሯል። ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችንን ለምን ‹ከሕግ በታች የተወለደ› አለው ቢባል ሁለት አይነት ሕግ አለ። የመጀመሪያው ሕግ ጠብዓያዊ እና ሕግ መንፈሳዊ ናቸው።

- **ሕግ ጠብዓያዊ** ማለት የተፈጥሮ ሕግ ማለት ነው፤ ዘጠኝ ወር በማሕፀን መቆየት፣ ቀስ በቀስ እንደ ሕፃናት ማደግ ... ማለት ነው።
- **ህግ መጽሐፍዊ ማለት** በሙሴ የሕግ መጻሕፍት ላይ የተጻፉትን መፈጸም ማለት ነው። ለምሳሌ፡- በሥምንተኛው ቀን ግዝረት መፈጸም፣ በ12 ዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም መሔድ፣ በ30 (ሠላሳ) ዓመቱ መጠመቅ፣ እነዚህን የመሳሰሉትን ሌሎችንም ማለት ነው። ከሕግ በታች ሲል እርሱ ልዑለ ባሕርይ ሲሆን የሕግ ሁሉ አስገኚ ሲሆን እንደ ሰው ሕግን እየፈጸመ አደገ ማለት ነው። አምላክ ነኝ ብሎ በአንድ ቀን ተፀንሶ አልተወለደም፣ አላደገም፤ እንደ ሰው ቀስ በቀስ አደገ እንጂ *‹‹ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ ይታዘዝላቸውም ነበር፤ እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር፤ ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር››* ሉቃ፡-2÷51-52 እራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር *‹‹እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም››* ማቴ፡-5÷17 በማለት ተናግሯል።

ውድ ተማሪያችን ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው የማይጨበጠው ረቂቁ መራብ፣ መጠማት፣ መታመም፣ መሞት፣ የማይስማማው የፍጡራን ዕውቀት መርምሮ የማይደርስብት የሕይወት መሠረት የሆነው የመለኮት አካልና ባሕርይ ውሱን፣ ግዙፍና የሚጨበጥ፣ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ የተገኘውና መራብ፣ መጠማት፣ መታመም፣ መሞት የሚስማማውን አካል እነዚህ ሁለት ነገሮች ከተዋሕዶ በኋላ አንድ ሆነዋል። ይህም ማለት አምላክ ሰው የሆነው በተዋሕዶ

ነው ማለት ነው። ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት የሚባል ነገር የለም፤ መለኮት ርቀቱን ለቅቆ፣ ሳይገዝፍ፣ ሳይለወጥ፣ እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ እንጂ። ሥጋም ግዝፈቱን ለቅቆ ረቀቀ ጠፋ አይባልም፤ ሁለቱም አንድ ሆነዋል እንጂ። *‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበረ››* ዮሐ፡-1÷1 በማለት የቃልን ቅድምና ከተናገረ በኋላ *‹‹ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ››* ዮሐ፡-1÷14 በማለት የቃልን ከሥጋ ጋር መዋሐድ ይናገራል። ቅዱስ ጳውሎስም ስለተዋሐዶ ታላቅነት ሲናገር *‹‹እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው››* በማለት ተናግሯል 1 ጢሞ፡-3÷16። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያስረዳ *‹‹እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሐደ ... ››* ኤፌ፡-2÷14 በማለት ሥጋና መለኮት መዋሐዳቸውን ተናግሯል።

ውድ ተማሪያችን እዚህ ጋር አንድ መገንዘብ የሚኖርብን ነገር ከተዋሕዶ በኋላ መለኮትና ሥጋ ለዓይን ጥቅሻ ለከንፈር ንክሻ ያህል እንኳን አልተለያዩም። በፍጹም ተዋሕዶ አንድ ሆኑ እንጂ። ቅዱስ ቄርሎስ ከተዋሕዶ በኋላ ሁለትነት እንደሌለ ሲናገር ማለትም እንደሌለብን ሲያስጠነቅቀንም *‹‹ከተዋሕዶ በኋላ ስለ ሁለት ባሕርያት እንናገር››* ብሎአል። ታዲያ ተዋሕዶ እንደምንድን ነው? ቢባል፡-

- **እንበለ ውላጤ**፦ ውላጤ ማለት መለወጥ ማለት ነው፤ አንዳንድ ሰዎች (መለኮት ተለውጦ ሥጋ ሆነ› የሚሉ አሉና፤ ለምሳሌ ብለው ‹የሎጥ ሚስት ወደ ጨው ዓምድነት እንደተለወጠች) ዘፍ፡-19÷23 የሚሉ አሉ። መለኮት ግን በባሕርይው መለወጥ የለበትም። አምላክም ሰው ሆነ ስንል ያለመለወጥ ነው።

- **እንበለ ኅድረት**፡- ኅድረት ማለት ማደር ማለት ነው፤ እንደ ሰይፍና ሰገባ፣ እንደ ዳዊትና ማኅደር። *‹በእኛ አደረ›* የሚለውን ወስደው መለኮት በሥጋ ላይ አደረ የሚሉ አሉና። ለተዋሕዶ ግን እንዲህ ተብሎ አይነገርም፤ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያስረዳ *‹‹እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሐደ ...››* ኤፌ፡-2÷14 በማለት ሥጋና መለኮት መዋሐዳቸውን አንድ መሆናቸውን አንዱ በአንዱ እንዳላደረ ተናግሮአል።

- **እንበለ ቱሳሔ**፡- ቱሳሔ ማለት መቀላቀል፣ መደባለቅ ማለት ነው። ሁለቱም ተደባልቀው ከሁለቱም ትንሽ ትንሽ መውሰድ፣ እንደ ወተትና ቡና ሲደባለቅ መልክ ማዕከላዊ ጣዕም መዕከላዊ እንደሚያመጣ ብለው የሚናገሩ አሉ፤ መለኮትና ሥጋ ያለመቀላቀል አንዱ አንዱን ሳያጠፋ በተዋሕዶ አንድ ሆነዋል።

- **እንበለ ትድምርት፡-** ትድምርት ማለት መደራረብ ማለት ነው፤ እንደ አነባብሮ እንጀራ በእንጀራ ላይ እንደሚደራረብ እንዲሁ መለኮት በሥጋ ላይ ተደረበ የሚሉ አሉና። ይህም ስህተት ነው አምላክ ሰው ሲሆን ያለመደራረብ ነው።



ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሲሆን ከላይ እንደጠቀስናቸው ያለሚጠት፣ ያለ ኅድረት፣ ያለ ቱሳሔ፣ ያለትድምርት በተዋሕዶ ነው።



ታዲያ ተዋሕዶ ማለት ምን ማለት ነው?

_____

_____

**በተዋሕዶ** ማለት በተገናዝቦ አንድ ሆነ፣ ምንታዌነትን (ሁለት መሆንን) አጠፋ ማለት ነው። ይህም ‹ተዋሐደ› - ‹አንድ ሆነ› ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙ አንድ መሆን፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ በሕርይ፤ ከሁለት አካል አንድ አካል ማለት ነው። ይህም በተዐቅቦ (በመጠባበቅ) ነው። መለኮት የሥጋን ባሕርይ ሳያጠፋ፤ ሥጋም የመለኮትን ባሕርይ ሳያጠፋ በመጠባበቅ ማለት ነው። ይህም ‹ይህ ለመለኮት›፣ ‹ይህ ለሥጋ› ሳይባል በአንድ አካል በአንድ ባሕርይ መገኘት ማለት ነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በመጥቀስ እንመልከት።

*‹‹ሲያልፍም ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ... ወደ መሬት እንትፍ ብሎ በምራቁ ጭቃ አድርጎ በጭቃው የእውሩን ዓይኖቹ ቀባና፦ ሒድና በሰሊሆም መታጠቢያ ታጠብ አለው ትርጓሜው የተላከ ነው፤ ስለዚህ ሔዶ ታጠበ እያየም መጣ››* ዮሐ፡-9÷1-8 እዚህ የተሠመረበት ቃል ላይ ስንመለከት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገና ሲወለድ ዓይን ያልነበረውን ሰው ሲፈውሰው እንመለከታለን፤ *‹በምራቁ ጭቃን አደረገ›* ይላል። እዚህ ጋር ሥጋ ነው ወይስ መለኮት እንዲህ ያደረገው? ቢባል፤ መቼም የሰው ምራቅ በጭቃ ተለውሶ ዓይን ሊያበራ አይችልም፤ መለኮት ነው እንዳንል ለመለኮት ምራቅ የለውም፤ ታዲያ በምን ሆነ? ቢባል በተዋሕዶ ነው። መለኮት የሥጋን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎ ሥጋም የመለኮትን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎ ነው እንጂ ለሥጋ ለመለኮት ተብሎ ተከፋፍሎ አይነገርም።

*‹‹ኢየሱስም ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው፤ እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው። አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው ሰጡትም። አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውኃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደመጣ አላወቀም››* ዮሐ፡-2÷7-9 እዚህም ጋር ስንመለከት እንደ ሰውነቱ በሠርግ ቤት ተጠራ፤ እንደ አምላክነቱ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅነት ቀየረ። ከሐዋርያቱ ጋር በታንኳ ሲሔድ መተኛቱና ማዕበሉን ጸጥ ማድረጉ (ማር፡-4÷35-41)፤ ከሞተ አራት ቀን የሆነውን አልዓዛርን ማስነሣቱ (ዮሐ፡-11÷38-45)

ውድ ተማሪያችን ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው በተዋሕዶ ጊዜ መለኮት እንዲህ አደረገ ሥጋ እንዲህ አደረገ ተብሎ አይነገርም በተዋሕዶ አንድ ሆነዋልና።

**ለምሥጢረ ተዋሕዶ ምሳሌ**

ሙሴ በኮሬብ ተራራ ያየው ሐመልማልና ነበልባል፡- *‹‹...እነሆም ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ››* ዘጸ፡-3÷2-3 ይህ የመለኮትና የሥጋን መዋሐድ የሚያሣይ ነው። ነበልባሉ ቁጥቋጦውን አለማቃጠሉ መለኮት ሥጋን ላለማጥፋቱ ምሳሌ ነው፤ ሐመልማሉ እሳቱን አለማጥፋቱ ሥጋ መለኮትን አለመወሰኑ (አለመጠቅለሉ) ምሳሌ ነው።

*እሳት የተዋሐደው ብረት (የጋለ ብረት)፡-* ቅዱስ ቄርሎስ መናፍቁ ንስጥሮስን ያሳፈረበት፣ ተዋሕዶን የገለጸበት ያስረዳበት ምሳሌ ነው።



# መልመጃ ሦስት

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ ስጡ

1. እግዚአብሔር ወልድ ስንት ልደታት አሉት? በዝርዝር ይግለጹ።

   _____

   _____

2. የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የስምዋ ትርጓሜ ምን ማለት እንደሆነ ይግለጹ?

   _____

   _____

3. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከተመሰለችባቸው ምሳሌዎች መካከል ሦስቱን በመግለጽ በዝርዝር ያስረዱ?

   _____

   _____

4. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትወልደው ከመጽሐፍቅዱስ በመጥቀስ ይግለጹ?

   _____

   _____

5. ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ሰው እንደሆነ በዝርዝር ይግለጹ?

   _____

   _____

6. ተዋሕዶ ማለት ምን ማለት ነው?

   _____

   _____

# ምዕራፍ አራት
# ምሥጢረ ጥምቀት



## መግቢያ

ውድ ተማሪያችን ከዚህ በማስከተል በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢር መካከል አንዱ ስለሆነው ምሥጢረ ጥምቀት ‹ምሥጢር› መባልና የሚያሠጠውን መንፈሳዊ ጸጋ ከዚህ በታች ለመዘርዘር እንሞክራለን። እርስዎም በደንብ በማንበብና በማገናዘብ ዕውቀትዎን ያዳብሩ።

## ዓላማዎች

ይህን ምዕራፉ በሚገባ አጥንተው ከጨረሱ በኋላ:-

- የምሥጢረ ጥምቀትን ትርጉም ያብራራሉ፤
- ምሥጢረ ጥምቀት ለድኅነት ያለውን ቦታ ወይም ድርሻ ያስረዳሉ፤ እንዲሁም
- ስለ ሥርዓተ ጥምቀት (በውኃ ስለመፈጸሙ፣ በቅድስት ሥላሴ ስም ስለመጠመቃችን፣ ወዘተ) ያስረዳሉ::

## 4.1 የምሥጢረ ጥምቀት ትርጉም

ጥምቀት፡- ‹አጥመቀ›- ‹አጠመቀ› ካለው የግእዝ ግሥ የወጣ ነው። ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ በተጸለየበት ውኃ ‹ማየ ገቦ/ማየ ሕይወት› ውስጥ በሥላሴ ስም መጥለቅ፣ መዘፈቅ፣ መነከር ማለት ነው። ለሌሎቹ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የመግቢያ በር ነው። ማናቸውም መንፈሳዊ ሥራዎች በመንፈሳዊ ልደት ሊጀመሩ ይገባል፤ ይህ መንፈሳዊ ልደት የሚገኘው ደግሞ በጥምቀት ነው። የክርስቶስ የሞቱና የትንሣኤው ምሳሌም ነው። ሮሜ፡-6፣3-5 በመሆኑም ወደ ውኃው 3 ጊዜ መጥለቃችን ጌታችን በከርሠ መቃብር 3 (ሦስት) ቀን 3 (ሦስት) ሌሊት ማደሩን ከውኃው መውጣታችን ደግሞ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው።\

## 4.2 ጥምቀተ ክርስቶስ

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠላሳ ዘመኑ፣ በዮሐንስ እጅ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቋል። የተጠመቀበትም ዕለት ማክሰኞ ጥር 10 ለ11 አጥቢያ ከሌሊቱ በ10 ሰዓት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ያጠምቅ የነበረው የንስሓ ጥምቀትን ነበር፤ ጌታችን በእርሱ እጅ የተጠመቀው በደል ኖሮበት ይቅርታን ፈልጎ ሳይሆን በጥምቀቱ ጥምቀታችንን ሊያከብርልን አንድም ጌታው ከተጠመቀ ሎሌውም ይጠመቃልና እርሱ እንደተጠመቀ እኛም እንድንጠመቅ አብነት ወይም ምሳሌ ሊሆነን ነው።

### 4.2.1 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ተጠመቀ?

- አብነት ለመሆን፡- በጥምቀቱ ጥምቀታችንን ሊያከብርልን፤ አድርጎና አሳይቶ አድርጉ ሊለን ማቴ፡-11፣29
- የዕዳ ደብዳቤያችንን ለመደምሰስ (ቆላ፡-2፣14) *‹በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው›* የዕዳ ጽሕፈት የተባለው *‹‹አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ፤ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ . . . አዳም የዲያብሎስ ባርያ፤ ሔዋን የዲያብሎስ ገረድ››* የሚለው ጽሑፍ ነበር። ይህንን ጽሑፍ ዲያብሎስ አዳምንና

ሔዋንን በዕብነ ሩካብ አጽፎአቸዋል፤ ከዚያም አንዱን በሲያል አንዱን በዮርዳኖስ ወንዝ አስቀምጦታል። ይህንን የጠላትን ጥበብ የሚያውቅ ጌታ በዮርዳኖስ የነበረውን በጥምቀቱ፤ በሲያል ያኖረውን ደግሞ በስቅለቱ ጊዜ አጥፍቶልናል።

- በምሳሌ ብቻ ይታወቅ የነበረውን ምሥጢረ ሥላሴ ለመግለጥ፤ በብሉይ ዘመን እግዚአብሔር ስለአንድነቱ እንጂ ስለሦስትነቱ በምሳሌ ወይም በራእይ እንጂ በግልጥ አላሳየም ነበርና ይህንን ልዩ የሆነውን ምሥጢር በጊዜ ጥምቀቱ ገልጦልናል። በተለየ አካሉ እግዚአብሔር ወልድ በባሕረ ዮርዳኖስ ሲጠመቅ እግዚአብሔር አብ በደመና ከሰማይ ሆኖ *‹የምወድደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት›* የሚል ምስክርነት ሲሠጥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል በላዩ ላይ በማረፍ አንድነቱ ሦስትነቱን የማይጠቀልለው ሦስትነቱ አንድነቱን የማይከፋፍለውን የሥላሴን ልዩ አንድነትና ሦስትነት ምሥጢር አየን። ማቴ፡-3፣17

## 4.2.2 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በሠላሳ ዘመኑ ተጠመቀ?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ30/ሠላሳ/ ዘመኑ መጠመቁ እኛንም *‹በ30/ሠላሳ/ ዘመናችሁ ተጠመቁ›* ሊለን ሳይሆን በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡-

- 30/ሠላሳ/ ዘመን ሙሉ ሰው የሚሆኑበት፣ ለምግባር ለትሩፋት የሚበረቱበት በመሆኑ በ30/ሠላሳ/ ዘመኑ በመጠመቅ ጥምቀትን የሥራው መጀመሪያ አደረገ፤ እርሱ ሊቀካህናት፣ መመህርና አዳኝ ነውና። በብሉይ ኪዳን ለአገልግሎት የሚወጡት፣ ለክህነት የሚበቁት በ30/ሠላሳ/ ዘመናቸው ነበር፤ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ እንኳን ከ20/ሃያ/ እና 25/ሃያ አምስት/ በፊት አይወጡም ነበር። ዘኅC፡-4፣35፣ 2 ሳሙ፡-5፣4፣ ዘኅC፡-3፣4፣ 1 ዜና፤-23፣24፣ 1 ጢሞ፡-3፣6-10
- የቀደመው ሰው አዳም የ30/ሠላሳ/ ዘመን ጎልማሳ በመሆን ተፈጥሮ ልጅነትን አግኝቶአል፤ መልሶ ይህን ልጅነት በኃጢአት ምክንያት አጥቶታል፤ ዳግማዊ አዳም ጌታችንም በ30/ሠላሳ/ ዘመኑ ተጠምቆ የአዳምን የልጅነት ጸጋ መልሶለታል።

## 4.2.3 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በዮርዳኖስ ተጠመቀ?

- በዮርዳኖስ ተጥሎ የነበረውን የዕዳ ጽሕፈት ለመደምሰስ፡- ቈላ፡-2፣14 *‹‹በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው»* የዕዳ ጽሕፈት የተባለው *‹‹አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ፤ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ . . . አዳም የዲያብሎስ ባርያ፤ ሔዋን የዲያብሎስ ገረድ››* የሚለው ጽሑፍ ነበር። ይህንን ጽሑፍ ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን በዕብነ ሩካብ አጽፎአቸዋል፤ ከዚያም አንዱን በሲያል አንዱን በዮርዳኖስ ወንዝ አስቀምጦታል። ይህንን የጠላትን ጥበብ የሚያውቅ ጌታ በዮርዳኖስ የነበረውን በጥምቀቱ፤ በሲያል ያኖረውን ደግሞ በስቅለቱ ጊዜ አጥፍቶልናል።
- ትንቢትና ምሳሌን ለመፈጸም፡- መዝ፡-76፣16 *‹‹አቤቱ ውኆች አዩህ፤ ውኆችም አይተውህ ፈሩ፤ ጥልቆችም ተነዋወጡ፤ ውኆችም ጮኹ››*፤ መዝ፡-113፣3 *‹‹ባሕር አየች ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደኋላው ተመለሰ፤ ተራሮች እንደኮርማዎች ኮረብቶችም እነደ ጠቦቶች ዘለሉ››* ‹ተራሮች›- ቅዱሳን ሐዋርያት፣ ‹ኮረብቶች›- ቅዱሳን አርድእት ናቸው።
- የዮርዳኖስ ወንዝ ከመነሻው አንድ ሆኖ ይመጣና በኋላ ላይ ይከፈላል፤ እንደገናም መልሶ ይገናኛል። ጌታችን የተጠመቀው የተለያዩት የዮርዳኖስ ወንዝ ክፍሎች በሚገናኙበት ቦታ ላይ ነው። ወንዙ አንድ ሆኖ መምጣቱ የሰው

ዘር በሙሉ ከአንዱ አዳም የመገኘቱ፤ ለሁለት መከፈሉ- በመገረዝና ባለመገረዝ ሕዝብና አሕዛብ ተብሎ ለሁለት መከፈሉን፤ ጌታችን የተለያዩት ወንዞች በሚገናኙበት ቦታ መጠመቁ- ሕዝብና አሕዛብን አንድ ላደርግ መጣሁ ሲል፤ እንዲሁም እርሱ በትምህርትም በተግባርም የመሠረተልን ምሥጢረ ጥምቀት ለሕዝብም ለአሕዛብም የምትፈጸም መሆኗን ለማመልከት።

- የዮርዳኖስ ወንዝ እጅግ ሲሞላ ሦስት ሜትር እጅግ ሲጎድል አንድ ሜትር ይሆናል፤ ይህም የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ምሳሌ ነው።
- የዮርዳኖስ ወንዝ የነጻነት ምሳሌ ነው፤ እስራኤል ዘሥጋ ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት እንደገቡ እኛም በጥምቀት ልጅነትን አግኝተን ርስት መንግሥተ ሰማያትን እንወርሳለን ነው።

## 4.3 ጥምቀት ለምን በውኃ ይፈጸማል?

ጥምቀት የሚለው ቃል በራሱ የሚያመለክተን መነከርን መረጨትን በመሆኑ ጥምቀት በውኃ ሊፈጸም ይገባዋል። በውኃ መፈጸም እንዲገባው የሚከተሉት ምክንያቶች ያስረዱናል፡-

- ራሱ ጌታችን በውኃ ተጠምቋልና ማቴ፡-3፣16 *‹ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ . . . ›*
- ትንቢተ ነቢያት ይፈጸም ዘንድ ሕዝ፡-36፣25 *‹ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ፤ እናንተም ትጠራላችሁ፤ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ›* ሚክ፡-7፣19 *‹ተመልሶ ይምረናል፤ ክፋታችንንም ይጠቀጥቃል፤ ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል›*
- በውኃ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሚሰፍፍ ዘፍ፡-1፣2 *‹‹የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር››*
- ጌታችን በውኃ እንድንጠመቅ ስላዘዘን ዮሐ፡-3፣5 *‹እውነት እውነት እልሃለሁ፡- ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም›*
- ሐዋርያት በውኃ አጥምቀዋልና የሐዋ፡-8፣38 *‹ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፤ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ፣ አጠመቀውም›*
- ንጉሥ ፈርያን በውኃ ድል እንደተነሣ በውኃ ተጠምቀንና የእግዚአብሔር ልጆች ተሰኝተን ኃጢአትን ሁሉ ድል እንደምንነሣ ለማመልከት ዕብ፡-11፣29
- የቀድሞ ሰዎች በውኃ ጥፋት ደርሶባቸው ነበርና ውኃ ለምሕረት መፈጠሩን ይጠራጠሩ ነበር፤ ማለትም ለመርገም ብቻ እንደተፈጠረ አድርገው ያስቡና ያምኑም ነበር። ውኃ ለምሕረትም መፈጠሩን ለማመልከት ዘፍ፡-8፣12
- ውኃ መንጽሔ እድፍ ነው፤ ማለት ከእድፍ ያነጻል፣ ያጠራል፤ በጥምቀትም ከነፍስና ከሥጋ ገርስቄልና እንደምንጠራ፣ እንደምንነጻም ለማመልከት
- ውኃ በሁሉም ቦታ ይገኛል፣ ለድሃም ለሀብታምም እኩል ነው። ጥምቀትም ለሁሉም (ለሕዝብም ለአሕዛብም፤ ለድሃም ለሀብታምም) እኩል የምትፈጸም መሆኗን ለማመልከት
- ውኃ መልክን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፤ እኛም በውኃ ተጠምቀን የሥላሴን መልክ በመንፈስ እናያለንና
- እሳት ምንም ያህል ቢበረታ በውኃ ይጠፋል፤ እኛም በውኃ ተጠምቀን አስፈሪ ከሆነ ከገሃነመ እሳት እንድናለን ስንል ማር፡-16፣16
- ውኃ ያለመልማል፤ እኛም በውኃ ተጠምቀን የሥጋና የነፍስን ልምላሜ እናገኛለን ስንል
- ውኃ ውኂዝ (ፈሳሽ) ነው፤ በዚህም ምክንያት ከአጽናፍ አጽናፍ ይደርሳል፤ ጥምቀትም በሁሉ ያለች መሆኗን ለማመልከት
- ውኃ ተዋስያን (ጥቃቅን ነፍሳት) አይቀርቡትም፤ በውኃ ጥምቀት ሰውነቱ የከበረ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ርከርሳት መናፍስት አይቀርቡትምና ነው

## 4.4 የክርስቲያኖች ጥምቀት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖችን በተወለዱ በ40 እና በ80 ቀን ታጠምቃለች። ነገር ግን ከሌላ እምነት ለሚመጡ በማንኛውም የዕድሜ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰዎች ሥርዓት ሠርታ ጥምቀትን ትፈጽማለች። ይህንም ለሁለት ከፍለን የሕፃናት እና የንዑሰ ክርስቲያን ጥምቀት ብለን መመልከት እንችላለን።

### 4.4.1 የሕፃናት ጥምቀት

ሕፃናት የሚጠመቁት የቤተሰቦቻቸውን /የወላጆቻቸውን/ እምነት መሠረት በማድረግ ነው። ቅዱሳን ሐዋርያት በነበሩበት ዘመን የሚያምኑ ሰዎችን ያጠምቁ የነበሩት ከነቤተሰቦቻቸው ነበር። ይኸም ቤተሰቡ በሙሉ ባመነው ሰው እምነት መሠረትነት ይጠመቅ ነበር ማለት ነው። የሐዋ፡-10፣1 (የቆርኔሌዎስ ከነቤተሰቡ መጠመቅ)፤ የሐዋ፡-16፣14-15 (የልድያ ከነቤተሰቧ መጠመቅ) እስራኤል ከባርነት ነጻ ሲወጡ ሕፃናት ዐዋቂ፣ ወንድ ሴት ሳይባል ቀይ ባሕርን ተሻግረው ርስትን ወርሰዋል። ይህ ምሳሌው የሆነለትም ጥምቀትም በቤተክርስቲያን ያለ እድሜ ልዩነት ሁሉም የመንግሥተ እግዚአብሔር ወራሽ እንዲሆን ለሁሉ ይፈጸማል። 1 ቆሮ፡-10፣1-5
የመንፈስቅዱስ ተስፋ - ተስፋ ድኅነት የተሠጠው ለዐዋቂዎች ብቻ አይደለም፤ ለሁሉም እንጂ። የሐዋ፡-2፣38 *‹ንስሓ ግቡ ኃጢአታቸሁም ይሠረይ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ሥጦታ ትቀበላላቸሁ›* ይህ ተስፋ ሕፃናትንም እንደሚጨምር መገንዘብ ያሻል።

ሕፃናቱ ሳያምኑ ሳይጠመቁም ቢሞቱ ከልጅነት ጸጋ ውጪ ናቸውና አባት ሊሆናቸው የሚችል የእግዚአብሔርን ምሥጢር ሊያውቁ አይችሉም፤ ከርስቱም አይካፈሉም። በተጨማሪም ጥምቀት ለሌሎቹ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ቀዳሚ/መግቢያ ናትና ባለመጠመቃቸው ሌሎቹንም ምሥጢራት ያጧቸዋል። ዮሐ፡-6፣53

### 4.4.2 የሕፃናት ጥምቀት ለምን በ40 እና በ80 ቀናት ሆነ?

- የመጀመሪያው ሰው አዳም ወደ ገነት በ40ኛው ቀን ሔዋን ደግሞ በ80ኛው ቀን ገብተዋል። ኩፋ፡-4፣9 *‹በተፈጠረባት ምድር ለአዳም አርባ ቀን ከተፈጸመለት በኋላ ይገዛትም ይጠብቃትም ዘንድ ወደ ገነት አስገባነው፤ ሚስቱንም በሰማንያ ቀን አስገባናት›* ሕፃናትም እንደየጾታቸው ወንዶች በተወለዱ በዐርባ ቀናቸው ሴቶችም በሠማንያ ቀናቸው ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃቸው ጥምቀት ይፈጸምላቸዋል።
- የኦሪትን ሕግና ሥርዓት መሠረት በማድረግ ዘሌ፡-12፣1-8 *‹ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅንም ብትወልድ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት፤ እንደ ሕመምዋ መርገም ወራት ትረክሳለች። በሠምነተኛው ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ፡ ፡ ከደምዋ እስክትነጻ ሠላሳ ሦስት ቀናት ትቀመጥ* (ሰባትና ሠላሳ ሦስት ዐርባ መሆኑን ያስተውሉ) *. . . ሴት ልጅም ብትወልድ እንደመርገምዋ ወራት ሁለት ሣምንት ያህል የረከሰች ናት፤ ከደምዋም እስክትነጻ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ* (ሁለት ሣምንት ማለት ዐሥራ ዐራት ቀናትና ስድሳ ስድስት ቀናት ሠማንያ ቀናት ይሆናሉ)፡፡

### 4.4.3 የንዑሰ ክርስቲያን ጥምቀት

ንዑሰ ክርሰቲያን - የክርስቲያን ታናናሾች ማለት ነው። ሳያምኑ የቆዩ፣ ያልተጠመቁ፣ ኋላ ግን የቤተክርስቲያንን እምነት፣ ዶግማና ቀኖና አምነውና ተቀብለው ለመጠመቅ የቀረቡ በየትኛውም እድሜ ላይ የሚገኙ ሰዎች ናቸው።

 ንዑሰ ክርስቲያን ለጥምቀት ምን ያስፈልጋቸዋል?

_____

_____

ንዑሰ ክርስቲያን ለጥምቀት:-

- **ትምህርት**፡-ማቴ፡-28፣19 *‹እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ . . . ያዘዝኋቸሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራቸኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው›፤* ሮሜ፡-10፣17 *‹እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው›*
- **እምነት:-** የሐዋ፡-16፣14-15 *‹ልድያ የሚሏት አንዲት ሴት ትሰማ ነበር . . . በጌታ የማምን እንድሆን ከፈረዳቸሁልኝ ወደ ቤቴ ገብታችሁ ኑሩ ›*
- **ንስሐ:-** የሐዋ፡-2፣37 *‹ንስሓ ግቡ ታጠኢአታቸሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳቸሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ›*

አንድ ንዑሰ ክርስቲያን ከመጠመቁ በፊት ለሦስት ዓመት ያህል በማኅበር ጸሎት ይካፈላል፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ይማራል፣ ንስሓውን ወይም ቀኖናውን ይፈጽማል። ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ ይጠመቃል።

ጥምቀት በሥላሴ ስም ይፈጸማል፡- ማቴ፡-28፣19 *‹አሕዛብን ሁሉ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃቸኋቸው...›* እንዲል። በሥላሴ ስም መጠመቃችን ልዩ ድንቅ የሚሆን አንድትና ሦስትነቱን የማመናችን ምልክትና መገለጫ ነው።
ሐዋርያት ስለምን *‹በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ›* የሐዋ፡-2፣37 አሉ፡- ጥምቀቱን ሲፈጽሙ በሥላሴ ስም ነው፤ በዚህ ቦታ ላይ ግን ሕዝቡን ሲያዝዙ ‹በክርስቶስ ስም . . . › ማለታቸው በሚከተሉት ምክንያት ነው፡-

- ለምስክርነት - የባሕርይ አምላክነቱን ሊመሰክሩ
- በክርስቶስ ክርስቲያን ተባሉ ሲሉ የሐዋ፡-11፣26 *‹ደቀመዛሙርትም ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ›*
- ምሥጢረ ሥላሴ ለሕዝቡ ገና ግልጥ አልነበረምና፡- በብሉይ ዘመን እግዚአብሔር ስለአንድነቱ እንጂ ስለሦስትነቱ በምሳሌ ወይም በራእይ እንጂ በግልጥ አላሳየም ነበርና ይህንን ልዩ የሆነውን ምሥጢር በጊዜ ጥምቀቱ ገልጦልናል፡ ፡ በተለየ አካሉ እግዚአብሔር ወልድ በባሕረ ዮርዳኖስ ሲጠመቅ እግዚአብሔር አብ በደመና ከሰማይ ሆኖ ‹የምወድደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት› የሚል ምስክርነት ሲሠጥ እግዚአብሔር መንፈስቅዱስም በርግብ አምሳል በላዩ ላይ በማረፍ አንድነቱ ሦስትነቱን የማይጠቀልለው ሦስትነቱ አንድነቱን የማይከፋፍለውን የሥላሴን ልዩ አንድነትና ሦስትነት ምሥጢር አየን። ማቴ፡-3፣17 ይህ የሥላሴ ሦስትነት ለሕዝቡ ግልጥ አልነበረምና ለጊዜው በሚያውቁት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ ሕዝቡን አዘዙ።
- አምላክነቱን ክደው ሰቅለውት ነበርና አምላክነቱን ማመናቸውን ለማረጋገጥ
- የክርስቶስ ስም ሲጠራ የአብም የመንፈስቅዱስም ስም ይጠራልና ነው

## 4.5 ጥምቀት አንዲት ናት

- ሰው ከእናት ከአባቱ አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚወለድ ከእግዚአብሔርም አንድ ጊዜ በጥምቀት ይወለዳል።
- የቃለ እግዚአብሔር ምስክርነት ኤፌ፡-4፣5 *‹አንድ ጌታ፤ አንዲት ሃይማኖት፤ አንዲት ጥምቀት› ፤ ‹ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል›* ማር፡-16፣16



# መልመጃ አራት

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ ስጡ

1. ጥምቀት የሚለው ቃል የምን ቃል ነው ትርጉሙስ ምን ማለት ነው?

   _____

   _____

2. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ? አብራሩ።

   _____

3. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ተጠመቀ?

   _____

   _____

4. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በ30 ዓመቱና በዮርዳኖስ ተጠመቀ?

   _____

   _____

5. ጥምቀት ለምን በውኃ ይፈጸማል? አብራርተው ይግለጹ።

   _____

   _____

6. ቅድስት ቤተክርስቲያን ሕፃናትን ለምን በሕፃንነታቸው እና በ40 እና በ80 ቀናቸው ታጠምቃለች?

   _____

   _____

7. አንድ ንዑሰ ክርስቲያን ለመጠመቅ የሚያስፈልገው ነገር ምንድን ነው?

   _____

   _____

8. ጥምቀት አንዲት የሆነችበትን ምክንያት ምን እንደሆነ አብራርተው ይግለጹ?

   _____

   _____

# ምዕራፍ አምስት
# ምሥጢረ ቁርባን



## መግቢያ

የተከበሩ ውድ ተማሪያችን ጌታችን በወንጌል ላይ ሲናገር *‹‹ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው››* ዮሐ፡-6፤51-57 ባለው መሠረት ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ስለ ምሥጢረ ቁርባን እንማማራለን። ስለ ቅዱስ ቁርባን አመሠራረትና ስለ ሌሎቹም ነገሮች አያይዘን ጠቅሰናል፤ እርስዎም ትኩረት በመስጠት እያነበቡ ሌሎችን መጻሕፍት በማገናዘብ ዕውቀትዎን ያዳብሩ፤ መልካም የንባብ ጊዜ።

## ዓላማዎች

ይህን ምዕራፉ በሚገባ አጥንተው ከጨረሱ በኋላ:-

- ✧ የምሥጢረ ቁርባንን ትርጉምና አመሠራረት ያብራራሉ፤ እንዲሁም
- ✧ ምሥጢረ ቁርባን ለድኅነተ ነፍስ ያለውን ድርሻ ገልጸው ያስረዳሉ፤
- ✧ ስለ ሥርዓተ ቁርባን ያብራራሉ፤ በተጨማሪም
- ✧ ስለ ምሥጢረ ቁርባን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ምሳሌያትን አብራርተው ይገልጻሉ::

## 5.1 የምሥጢረ ቁርባን ትርጉምና አመሠራረት

ቁርባን፡- የሚለው ቃል የሱርስት ሲሆን ትርጓሜውም ‹መንፈሳዊ አምኃ› ማለት ነው። ‹ቀርበ› ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ተደርጎ ሲተረጎም ‹መቀራረቢያ› የሚል ፍቺም ይሰጣል። (ይህ ከቁርባን አገልግሎት ወይም ከሚያሠጠው ጸጋ ጋር የተያያዘ ትርጓሜ ነው) በአጠቃላይ ቁርባን ማለት ‹መብዓ ሆኖ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ› ማለት ነው።



**ምሥጢረ ቁርባን፡-**

- ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት የሚሆንበት ምስጢር ነው
- ቅዱስ ሥጋውን በልተን ክቡር ደሙን ጠጥተን ለክብር የሚሆን የዘለዓለም ሕይወት ለማግኘት ክርስቶስን ለብሰን ተዋሕደን የምንኖርበት ታላቅ ምሥጢር ነው
- ጌታችን በዕለተ ዓርብ ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ፣ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ ሆኖ በመስቀል ላይ የፈጸመው የመቀራረብ ምሥጢር ነው
- ለራቁ ማቅረቢያ የሰላም ማሳደሪያ ነው ኤፌ፡2፣13

## 5.2 አመሠራረት

በሕገ ልቡና የነበሩ ደጋግ አባቶች ከእግዚአብሔር ለመታረቅ እርሱንም ደስ ለማሰኘት መሥዋዕትን በፈቃዳቸው ያቀርቡ ነበር፤ በዚህም ዘመን የመጀመሪያው መሥዋዕት አቅራቢ አዳም ነበር። ኩፋ፡-5፣1 ያቀረቡትም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የመገዛታቸውም ምልክትም ነበር። በዚህ ዘመን ከነበሩ አባቶች መካከል አቤል፣ ኖኅ፣ አብርሃም ወዘተ ሲገኙበት በኅብስትና በወይን መሥዋዕት ያቀርብ የነበረው መልከጼዴቅ ተጠቃሽ ነው። በዚህ ዘመን ይቀርቡ ነበሩት

መሥዋዕቶች ይልቁንም የመልከጼዴቅ መሥዋዕት ለአማናዊው መሥዋዕት ለቅዱስ ቁርባን ምሳሌ ነበር። እኒህ አባቶች ባቀረቡት መሥዋዕት ወደ ሲዖል ከመውረድ አልዳኑም፤ የዘለዓለም ሕይወትንም መውረስ አልቻሉም፤ የፍጡር ደም ፍጡርን ማዳን አይቻለውምና።

ከሕገ ልቡና ቀጥሎ በተተካው የሕገ ኦሪት ዘመን መሥዋዕት ማቅረብ ሕግ/ትእዛዝ ሆኖ በሙሴ አማካይነት ለሕዝበ እስራኤል ተሠጥቶአል። መሥዋዕቱንም የሚያቀርቡ ከሌዊ ነገድ የተወለዱ ካህናት ብቻ ነበሩ። ዘኅር፡-3፣10 በዚህ ዘመን ዐሥራ ሦስት ያህል የሚደርሱ የመሥዋዕት ዓይነቶች ይቀርቡ ነበር፤ ከእነዚህም መካከል የሚቃጠል፣ የእህል፣ የድኅነት፣ የኃጢአት፣ የበደል መሥዋዕት ጥቂቶቹ ናቸው። መሥዋዕቱንም ለማቅረብ ዐራት ነገሮች ያስፈልጉ ነበር። እነዚህም የሚቀርበው መሥዋዕት፣ መሥዋዕት የሚቀርብለት (ይቅርታ የሚጠየቅለት)፣ መሥዋዕት አቅራቢ (አስታራቂ ካህን)፣ መሥዋዕት ተቀባይ (ይቅር ባይ፣ ዋጋ ከፋይ እግዚአብሔር) ናቸው።

በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን ብዙ ዓይነት መሥዋዕቶች ቢቀርቡም ፍጹም ድኅነትን ግን መስጠት አልቻሉም። ጊዜያዊ ተስፋ እና ድኅነት፣ *ሥጋዊ* በረከትና ጊዜያዊ ዕርቅ ግን ያሠጡ ነበር፤ ኖኅን መሥዋዕቱን ተቀብሎ *‹ከእንግዲህ ወዲህ ምድርን በንፍር ውኃ አላጠፋትምኝ* የሚል ቃል ሠጠው። (ዘፍ፡-8፣20-22፤ ዘፍ፡-9፣8-17)፤ አብርሃም መሥዋዕት ቢያቀርብ በዘሩ የምድር አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩ ቃል ኪዳን ገባለት (ዘፍ፡-18፣3-18)፤ መልከጼዴቅ በመሥዋዕቱ ስለክህነቱ ዘለዓለማዊነት ተነገረው (መዝ፡-109፣4)፤ ጊዜያዊ እንጂ ዘለዓለማዊ ፈውስና ድኅነት እንዳላሰጡ ሲመለከት ራሱን መሥዋዕት፣ መሥዋዕት አቅራቢና መሥዋዕት ተቀባይ አድርጎ በመስቀል ላይ ምሥጢረ ቁርባንን መሠረተ።

## 5.3 ቅዱስ ቁርባን በብሉይ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን ዘመን ስለ አማናዊው ቅዱስ ቁርባን የተነገሩ ትንቢቶች የተመሰሉ ምሳሌዎችም ነበሩ። ጥቂቶቹን ስንመለከት መዝ፡-39፣6 *‹መሥዋዕትንና ቁርባንን አልወደድህም፤ ሥጋን አዘጋጀኸልኝ፤ የሚቃጠለውንና ስለኃጢአት የሚቀርበውን መሥዋዕት አልሻህምኝ*፤ ምሳ፤-9፣1-5 *‹ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሰሶዎቿን አቆመች፤ ፍሪዳዋን አረደች፣ የወይን ጠጅዋንም ደባለቀች፣ ማዕድዋን አዘጋጀች . . .›* ይገኙበታል።

ከምሳሌዎቹም መካከል አብርሃም ኮሎዶጎሞርንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ነገሥታት ድል አድርጎ ከተመለሰ በኋላ መልከጼዴቅ ኅብስትና ወይን ይዞ ተቀብሎታል። ዘፍ፡-14፣17-19 በዚህ ታሪክ ላይ አብርሃም የምዕመናን፣ መልከጼዴቅ የጌታችን አንድም የካህናት፣ ኅብስቱና ወይኑ ደግሞ የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ ምሳሌ ነው። ሌላው የእስራኤል ሕዝብ በቃዴስ በረሃ ከሰማይ ደማና እየወረደላቸው የተመገቡት መና ነው። ዘጸ፡-16፣13-16 መናው የጌታችን ቅዱስ ሥጋና ደም፣ ደመናው የእመቤታችን፣ እስራኤል የምዕመናን ምሳሌ ናቸው። ደመናው እስራኤልን ከረሃበ ሥጋ ያዳነን መናን እንዳስገኘ ከእመቤታችንም ከረሃበ ነፍስ የሚያድን ቅዱስ ቁርባን ተገኝቷል።

እስራኤላውያን በግብፅ ምድር የተመገቡት የመጨረሻው ራት ለቅዱስ ቁርባን ልዩ ምሳሌ ሆኖ እናገኘዋለን። ዘጸ፡-12፣1-20 *ነውር የሌለበት*- በባሕርይው ጌታችን ፍጹም ነውር የሌለበት ነውና፤ *ሲመሸ ይረዱት*- ጌታችን በሐሙስ ዕለት ምሽት መያዙን፤ *ከመራራ ቅጠል ጋር ይብሉት*- ነገረ መስቀሉን እያሰቡ፣ ከመቀበላቸው በፊት አፋቸው ምሬት እስኪሰማው ድረስ ለ18 ሰዓታት ጾመው፣ ለሥጋቸው መራራ የሆነን ቀኖና ተቀብለውና ፈጽመው ከቅዱስ ቁርባኑ ይቀበሉ፤ *በእሳት የተጠበሰውን ይብሉ*- ነፍስ የተለየውን መለኮት የተዋሐደውን ቅዱስ ቁርባን ለመቀበላችን፣ *በግ*- የጌታችን፤ *እስራኤላውያን*- የምዕመናን ምሳሌ፤ *እስከ 14ኛው ቀን ድረስ ይጠብቁት*- ጌታችን ዐራት ቀናት መክረው በምሽት ይዘው

በአምስተኛው ቀን እንደሚሰቅሉት፤ *ፈጥናቸሁ ትበሉታላቸሁ-* ሞታችሁን እያሰባችሁ፣ ዛሬ ነገ ሳትሉ፣ ንስሓ ገብታችሁ ተቀበሉ፤ *በትር ይዛቸሁ-* መስቀሉን ይዛችሁ፤ *ኩፊት ደፍታቸሁ-* ጌታችን ስለእኛ ሲል በራሱ ላይ የደፋውን የሾህ አክሊል እያሰባችሁ፤ *ዝናር ታጥቃቸሁ-* ንጹሐን ሆናችሁ፤ *ጫማ ተጫምታቸሁ-* ምሥጢርንና ወንጌልን ተምራችሁ ተቀበሉ፤ *ጥሬውን አትብሉ-* ነፍስ ያልተለየው መለኮት ያለተዋሐደው ነው አትበሉ፤ *የተቀቀለውን/ በውኃ የበሰለውን አትብሉ-* በጌታ ሥጋ ላይ መፍረስ መበስበስ የለበትምና ነው፤ *አጥንቱን አትስበሩ-* ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ በሌሎቹ ላይ እንደሚደረግ የእርሱ አጥንት እንደማይሰበር (ዮሐ፡-19፣33)፣ እንደአርዮስ አጥንት የሚነካ ክፉ ንግግር አትናገሩ (ወልድ ፍጡር አትበሉ)፤ *ከራሱ ከጭኑ ከሆድ ዕቃው ብሉ-* ጌታችን ቀዳማዊ፣ ማዕከላዊና ደኃራዊ መሆኑን፤ *በፊታቸሁ የተረፋቸሁን በእሳት አቃጥሉት-* የተቻላችሁን መርምራችሁ የቀረውን አንተ ታውቃለህ ብላችሁ ለእሳት መንፈስቅዱስ ሥጡ፤ *አንዱ ቤት የተሠዋውን ሌላው ጋር አትውሰዱ-* አንዱ ቤተክርስቲያን የተሠዋውን ሌላው ቤተክርስቲያን ወስዶ ማቁረብ አይገባም ሲል፤ *ሰባት ሆነው ቢበሉት-* በንስሓ ፍጹማን ሆናችሁ፤ *ዐሥር ቢሆኑ-* በሃይማኖት በምግባር ምሉዓን ሆናችሁ፤ *ዐሥራ ሁለት ቢሆኑ-* በዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ትምህርት አምናችሁ የሚል ምሳሌና ምሥጢር አለው።

ነቢዩ ኢሳይያስ ከለምጽ የተፈወሰበት ፍሕም ኢሳ፡-6፣1 *መፈዐኩ-* የዲያቆናት ወይም የቀሳውስት፤ *ጾጠኩ-* የእርፈ መስቀል ወይም የሥልጣነ እግዚአብሔር፤ *ፍሕሙ* - የቅዱስ ቁርባን፤ *ነቢዩ ኢሳይያስ* - የምዕመናን፤ *ለምጽ* - የፍዳ የመርገም ምሳሌ ናቸው።

## 5.4 የምሥጢረ ቁርባን አገልግሎት /ጥቅም/

አማናዊው ቅዱስ ቁርባን በሐዲስ ኪዳን እጅግ ብዙ የሆኑ ጸጋዎች፣ ጥቅሞችና በረከቶች አሉት። የመጀመሪያውም ከዚህ ምሥጢር የተካፈለውን ሰው ለዘለዓለማዊ ሕይወት ማብቃት ነው (ዮሐ፡-6፣54)፤ ሌላው እርሱ ራሱን የወይን ግንድ ብሎ እኛን ቅርንጫፎች እንዳደረገን ከግንዱ ከጌታችን ጋር አንድ ሆነን ፍሬን ማፍራት በዚህ ምሥጢር ይገኛል (ዮሐ፡-15፣1)፤ በመንፈሳዊ ዕውቀት ማደግ በጸጋ እግዚአብሔር መበልጸግ (ዮሐ፡-6፣35-55)፤ የኃጢአት ሥርየትም በቅዱስ ቁርባን ይገኛል (ማቴ፤-26፣27)፤ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ሕይወት ውስጥ ይኖራል (ዮሐ፡-6፣56)፤ ከጌታችን ጋር ያለን አንድነት ከቅዱሳን ጋር የሚኖረን ኅብረት በዚህ ምሥጢር ይጸናል ይረጋገጣልም (1 ቆሮ፡-10፣17)።

## 5.5 ምሥጢረ ቁርባን በስንዴና በወይን የመሆኑ ምሥጢር

ቅዱስ ቁርባን በስንዴ/ኅብስትና በወይን ከሆነበት ምሥጢርና ምክንያት አንዱ ትንቢተ ነቢያትን ለመፈጸም ነው። መዝ፡-4፣7 *‹በልቤ ደስታን ጨመርህ፤ ከስንዴ ፍሬና ከወይን ከዘይትም ይልቅ በዛ›* መዝ፡-103፣15 *‹ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል›* ሲራ፡-29፣21፤ ሲራ፡-34፣26 ሌላው መልከጼዴቅ በኅብስትና በወይን መሥዋዕት ያቀርብ ነበርና ያንን ምሳሌ ለመፈጸም ነው። ዘፍ፡-14፣17-20 ጌታችንም ራሱን በወይን መስሎ ተናግሮአል። ዮሐ፡-15፣1 *‹እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ›* ጌታችንም ከእናቱ ከእመቤታችን ጋር ሲመገቡት የኖሩት ነውና በእውነት ሥጋውንና ደሙን መሥጠቱን ለማመልከት፤ አንድም ስንዴ ስብ/ሥጋ ይመስላል ወይንም ደም ይመስላልና በሚመስል ነገር ለመሥጠት፤ አንድም ስንዴ ልባም ሴት የየዘችው እንደሆነ ነውር የሌለበት የማይለወጥ ይሆናል (ነውር የሌለባት የማትለወጥ ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል)፣ ወይንንም ቢጥሉት ከዕለት ዕለት ኃይሉ እየጨመረ ይሔዳል (ኃይል የሚሆን ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል) በኅብስትና በወይን ሆኗል።

## 5.6 ቅዱስ ቁርባን በመብልና በመጠጥ የሆነበት ምክንያት

አዳም አባታችን በለስን በመብላት በመብል ጠፍቶ ከገነትም ወጥቶ ነበርና በወጣበት ነገር እንዲገባ በጠፋበት ነገር እንዲድን ለማድረግ (ዮሐ፡-6፣54)። ሌላው ምክንያት ደግሞ መብል ከሰውነት ይዋሐዳልና በጸጋ ተዋሕጃችሁ እኖራለሁ ለማለት፤ አንድም መብል መጠጥ ያፋቅራል ቅዱስ ቁርባንም የጌታችንን ፍቅር በልቡና ያሳድራልና ነው፤ አንድም የተራበን የተጠማን ሰው ቢያበሉት ቢያጠጡት ይወድዳልና በነፍስ ለተራብን ለእኛ ምግበ ነፍስ ይሆነን ዘንድ ቅዱስ ቁርባንን በመብልና በመጠጥ አድርጎታል።

## 5.7 ቅዱስ ቁርባን መታሰቢያ ሳይሆን አማናዊ ነው

*‹እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና፡- ስለእናንተ የሚሠጠው ሥጋዬ ይህ ነው፣ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ›* ሉቃ፡-22፣19-20 በመጀመሪያ ‹መታሰቢያ› እና ‹መታሰቢያዬ› የሚሉት ቃላት ልዩነት ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ‹መታሰቢያ› ቢል ራሱን ቁርባኑን መታሰቢያ ያሰኛል፤ ‹መታሰቢያዬ› ማለቱ ግን ቅዱስ ቁርባኑን በተቀበልን ጊዜ ሁሉ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሠጠንን እርሱን ጌታችንን ማሰብ እንዲገባን ያስረዳል። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ እንደተናገረ፡- *‹ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ይህንንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና›* 1 ቆሮ፡-11፣26 ይህንን ይዛ ቤተክርስቲያንም በሥርዓተ ቅዳሴዋ፡- *‹ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ . . . አቤቱ ሞትህን እንናገራለን›* ትላለች። በሌላም ወገን ‹መታሰቢያ› ቢሆን ኖሮ *‹የሥጋዬ የደሜ ምሳሌ/መታሰቢያ›* ይላል እንጂ እንዴት *‹ሥጋዬ ደሜ›* ይላል? (ሉቃ፡-22፣19-21)

**ስለ ምሥጢረ ቁርባን የአበው ምስክርነት**

ስለቅዱስ ቁርባን በተለያየ ዘመን የተነሡ የቤተክርሰቲያን አባቶች ተናግረዋል።

ታላቁ ሊቅ **ቅዱስ ባስልዮስ** እንዲህ ሲል ተናግሮአል፡- *‹ጌታዬ ናፍቆቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፡- በዚህ በቅዱስ ቁርባን በሥጋውና በደሙ መለኮት እንደተዋሐደው አውቃለሁ፤ ይህንንም ስላወቅሁ ከክብር ሁሉ ጋር የከበረ ሥጋህን ከሰማያዊ ክብሩ ጋር አከብረዋለሁ . . . የዓለም ሁሉ ፈጣሪህ ኪሩቤል ሱራፌል የሚሰግዱለህ ንጉሠ ነገሥት አንተ እንዳለህ አውቄ አምኜ እቀበለዋለሁ›*

**ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም**፡- *‹ለዓለሙ ሁሉ ሕይወት ለመሆን በቀራንዮ እንደተሠዋ ለድኅነታችንም የምንሠዋው ይህ ኅብስት የበሰለና የደረቀ የሚዳሰስና የሚነሣ እንደመታየቱም ምድራዊ ኅብስት የማይጠቅም አይደለም። የኃጢአትን እሾህነት የሚነቅል እሳተ መለኮት ነው እንጂ፤ አመጸኞችን የሚያጠፋ በላዒ ነው፤ ኃጥአንንም የሚያቃጥል ውዑይ ነው›*

**አባ ሕርያቆስም**፡- *‹ዛሬ በዚህች ዕለት በፍቅርና በትሕትና ግሩም በሚሆን በዚህ ምሥጢርና ቁርባን ፊት እቆማለሁ፤ በዚህ ማዕድና ቁርባን ፊት። መንፈሳቸውን ያረከሱ ሰዎች ሊቀበሉት የማይቻላቸው በእውነት ቁርባን ነው። በበግ በጊደርና በላም ደም እንደነበረው እንደቀደሙት አባቶች መሥዋዕት አይደለም፤ እሳት ነው እንጂ። ባለማመን ለሚቀበሉት ሰዎች ከአንቺ የተገኘው ጽዋዕ የሚያሰክርና የሚያፍገመግም የሚጥልም ነው›*



# መልመጃ አምስት

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ ስጡ

1. በኦሪት ዘመን መሥዋዕት ካቀረቡት አባቶች መካከል አሁን ላለው አማናዊው ቁርባን ምሳሌ የነበረው የማን ነው? በምንና በምን ያቀርብ ነበር?

   _____

   _____

2. *‹እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና፡- ስለእናንተ የሚሠጠው ሥጋዬ ይህ ነው፣ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ›* ሉቃ፡-22፣19-20 ‹ለመታሰቢያዬ አድርጉት› ሲል ምን ማለት ነው? አብራርተው ይግለጹ?

   _____

   _____

3. ቅዱስ ቁርባን ለምንድን ነው በወይንና በስንዴ የሆነው? በማብራራት ይግለጹ።

   _____

   _____

4. ቅዱስ ቁርባን በመብልና በመጠጥ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? በማብራራት ይግለጹ።

   _____

   _____

# ምዕራፍ ስድስት
# ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን



## መግቢያ

ውድ ተማሪያችን በዚህ ክፍለ ትምህርታችን ደግሞ የምንማማረው ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢር መካከል የሆነውንና የተስፋ ምሥጢር የሚባለውን ስለ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ይሆናል። ትንሣኤ ሙታን ማለት ምን ማለት ነው? ሰዎች በዕለተ ምጽአት ጊዜ በምን ዓይነት አነሣስ ነው የሚነሡት? እና ሌሎችንም ትምህርቶች በዚህ ክፍል ለመጥቀስ ሞክረናል። እርስዎም ሌሎች መጻሕፍትን በማንበብና አባቶችን በመጠየቅ ዕውቀትዎን የበለጠ ያዳብሩ፤ መልካም የንባብ ጊዜ።

## ዓላማዎች

ይህን ምዕራፉ በሚገባ አጥንተው ከጨረሱ በኋላ:-

- የምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን ትርጉም ያብራራሉ፤ እንዲሁም
- ለሰው ልጅ ስንት ዓይነት ትንሣኤ እንዳለው ያስረዳሉ፤
- ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን በምሳሌ ያስረዳሉ፤ በተጨማሪም
- በዳግም ምጽአት በክብር ለመነሣት አንድ ክርስቲያን ምን ማደረግ እንዳለበት ይገልጻሉ

### 6.1 የቃሉ ትርጉም

ትንሣኤ ሙታን ማለት ነፍስና ሥጋ ተለያይተው ከኖሩበት እንደገና ተዋሕደው በዕለተ ምጽአት የሚነሡበት ወይንም ከሞት በኋላ ነፍስና ሥጋ እንደገና ተዋሕደው የሚነሡበት ምሥጢር ማለት ነው።

በሌላ መልኩ ደግሞ ትንሣኤ ማለት መነሣት፣ ሕያው መሆን፣ እውነተኛ መሆን፣ በንጽሕና በቅድስና መኖር መጀመር፣ በአጠቃላይ የእግዚአብሔር መሆን፣ በዕውቀት በአእምሮ መመላለስ ማለት ነው። ሉቃ፡-15÷23፣ ራእ፡-20÷6። ስለ ትንሣኤ ስንናገር ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ቢኖር ስለ ሥጋ ትንሣኤ መናገራችን ነው፤ ምክንያቱም ነፍስ በባሕርይዋ የማትሞት፣ የማትፈርስና የማትበሰብስ ናት። ስለዚህ ትንሣኤ የሚደረገው ሥጋ ሞቶ ፈርሶ ይኖር ከነበረበት ከመቃብር በሥልጣነ እግዚአብሔር ተነሥቶ ከነፍስ ጋር በመዋሐድ ነው።

### 6.2 የትንሣኤ ዓይነቶች

ሐዋርያዊት የሆነችው ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን የሰው ልጅ ሁለት ዓይነት ትንሣኤዎች እንዳሉት ታምናለች፤ እነርሱም ትንሣኤ ልቡና እና ትንሣኤ ዘጉባኤ በማለት የሚታወቁ ናቸው።

#### 6.2.1 ትንሣኤ ልቡና

ትንሣኤ ልቡና ማለት የሰው ልጅ በሕይወቱ እያለ በኃጢአት ባርነት፣ በክፋትና በበደል ውስጥ በመኖር ከእግዚአብሔር በመለየት የሚኖረው ኑሮ ሞት ስለሆነ ከዚያ የሚነሣበት ወይም የሚወጣበት ትንሣኤ ልቡና በማለት

ይታወቃል፤ አንድም በዳግም ምጽአት ከመነሣታችን በፊት በንስሓና በጽድቅ አሁን የምንነሣው ትንሣኤ ማለት ነው። ለዚህ ትንሣኤ ልቡና ንስሓ፣ ጥምቀት እና ቁርባን ወሳኝ ናቸው። ምክንያቱም ጌታችን *‹ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በመጨረሻው ቀን ይነሣል›* በማለት ተናግሮአልና ነው። ዮሐ፡-6÷54፣ ሮሜ፡-6÷3፣ 1 ቆሮ፡-15÷29

ሌላው ትንሣኤ ልቡና ማግኛ መንገድ ሞት ከተባለ ኃጢአት በንስሓ መነሣት ነው። ለዚህ ነው የጠፋው ልጅ አባት ስለ ልጁ ሲናገር፡- *‹‹ይህ ልጅ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኗል››* ሉቃ፡-15÷24 በማለት የተናገረው። ይህም ማለት የመጀመሪያውን ሞት ድል አድርገን መነሣት የምንችለው በንስሓ ትንሣኤ /ልቡና/ሕሊና ሲኖረን ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ በኃጢአትና በበደል መኖርን (ትንሣኤ ልቡና የሌለውን) የመጀመሪያው ሞት በማለት ይጠቅሰዋል *‹‹በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውም››* ራእ፡-20÷6 በማለት ትንሣኤ ልቡናን የፊተኛ ትንሣኤ ብሎ ይጠራዋል።

### 6.2.2 ትንሣኤ ዘጉባኤ

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማለት በመጨረሻው ቀን የሞቱት ሁሉም በአንድ ላይ /በጉባኤ/ በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ የሚነሡበት ማለት ነው፤ ይህም እነ ነቢዩ ኤልያስ፣ እነ ኤልሳ፣ እነ ቅዱስ ጳውሎስ ካስነሷቸው የሚለይ ነው። የሰው ልጅ ከፈረሰ ከበሰበሰ፣ አራቱ ባሕርያት ከተለዩት፣ ነፍስና ሥጋው ከተለያዩ በኋላ በአንድ በመሰባሰብ የሚነሡበት ማለት ነው። ኃጥአን ለመከራና ለአሣር ጻድቃን ለዘለዓለም ሕይወትና ጽድቅ የሚነሡበት ነው። *‹‹በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት፤ እኩሌቶቹ ወደ ዕረፍትና ወደ ዘለዓለም ገርስቁልና››* ዳን፡-12÷2 በማለት ተናግሮአል፤ ጌታችንም ይህንን በወንጌል ሲናገር፡-

*‹‹በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምጹን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና››* ዮሐ፡-5÷28 በማለት ኃጥአን ለመከራና ለአበሳ ጻድቃን ለዘለዓለም ሕይወት እንደሚነሡ ተናግሮአል።

## 6.3 የሙታን አነሣስ እንዴት ነው?

*‹የሞትክ ሁሉ›* የሚል የአዋጅ ቃል በመላእክት አለቃ ሲነገር የሞቱት ሁሉ ካሉበት ተሰብስበው ይነሣሉ፤ ይህንን ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር እንዲህ በማለት ገልጾታል፡-

*‹‹ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምጽ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና››* 1 ተሰ፡-4÷16 ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ በመጽሐፈ ቅዳሴው (ቁጥር 9—11) ይህን ሲናገር ሦስት ጊዜ መለከት በመላእክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል እንደሚነፋና ሙታን ሁሉ እንደሚነሡ ይገልጻል፤ ይህም፡-

- የመጀመሪያው መለከት ሲነፋ፡- አውሬ የበላው፣ አፈር ትቢያ የሆነው፣ በባሕር ውስጥ የቀረው ሁሉ የራስ ቅል ባለበት ቦታ ይሰባሰባል።

- ሁለተኛው መለከት ሲነፋ፡- *ሥጋና* አጥንቱ በአንድ ላይ በመገጣጠም አንድ በመሆን ሳይንቀሳቀስ ትኩስ በድን እሬሳ ይሆናል።
- ሦስተኛው መለከት ሲነፋ፡- በአካል በምንናገርበት አንደበት፣ ነፍስና *ሥጋ* ተዋሕደው፣ መብላት መጠጣት፣ ማግባት መጋባት፣ መውለድ መዋለድ የማያስፈልገው፣ ሞት የሌለበት ሆኖ፣ በጎም ሆነ ክፉ ሥራውን ይዞ፣ ጻድቃን ወደ ገነት ኃጥአን ወደ ገሃነመ እሳት ይሔዳሉ።

## 6.4 ለትንሣኤ ሙታን የተነገሩ ትንቢቶችና ምሳሌዎች

ለትንሣኤ ሙታን በብሉይ ኪዳን ብዙ ትንቢቶችና ምሳሌዎች ተነግረዋል። ከዚህ በመቀጠል የተወሰኑትን እንመለከታለን።
*‹‹ሙታንህ ሕያው ይሆናሉ ሬሳዎቸህም ይነሣሉ ...ምድርም ሙታንን ታወጣለች››* ኢሳ፡-26÷19
*‹‹በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት፤ እኩሌቶቹ ወደ ዕረፍትና ወደ ዘለዓለም ገርስቋልና››* ዳን፡-12÷2
*‹‹ጌታ እግዚአብሔር ለእነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል፡- እነሆ ትንፋሽን አገባባችኋለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ››* ሕዝ፡-37÷5
*‹‹ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች፤ ነፍሴን በሲዖል አትተዋትምና፣ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውምና››* መዝ፡-15(16)÷9—10

**ምሳሌዎች፡-**

- በአቤል ሞት ሞታችን፣ በሄኖክ ዕርገት ደግሞ ሞተን እንደማንቀር፣ ትንሣኤ እንዳለን በዲያብሎስ መገዛት እንደቀረ አወቅን፣ አየን። ዘፍ፡-4÷8፤ ዘፍ፡-5÷24
- ኖኅ በጥፋት ውኃ ጌዜ ወደ መርከብ መግባቱ ለመሞታችን፤ ከመርከብ መውጣቱ ለመነሣታችን ምሳሌ ነው። ዘፍ፡-6÷7
- ሌላው አብርሃምና ሣራ ካረጁ፣ ሙቀት ልምላሜ ከተለያቸው በኋላ ልጅ መውለዳቸው ለትንሣኤ ሙታን ምሳሌ ነው፤ አብርሃምና ሣራ ካረጁ በኋላ ልጅ መውለዳቸው ሰው ከሞተ ከፈረሰ በኋላ የመነሣቱ ምሳሌ ነው። ዘፍ፡-21÷1-2

**የሥነ ፍጥረት ምሳሌ፡-**

- **ፀሐይ፡-** ከምሥራቅ መውጣቷ ለመወለዳችን፣ ወደ ምዕራብ መሔድዋ በዚህ ዓለም ለመኖራችን በምዕራብ መጥለቋ ለመሞታችን ተመልሳ በስተ ምሥራቅ መውጣትዋ የትንሣኤያችን ምሳሌ ነው።
- **ጨረቃ፡-** መወለዷ (ሙሉ ሆና መውጣቷ) ለመወለዳችን፣ ማደጓ በዚህ ዓለም ላለን ሕይወት፣ ጠፍ መሆኗ ለመሞታችን፣ ዳግም መወለዷ የትንሣኤያችን ምሳሌ ነው።
- **እህል (ስንዴ)፡-** ስንዴ መዘራቱ ለመሞታችን፣ መበስበሱ የመቃብራችን ወይም የመበስበሳችን፣ ለመልሶ ማደጉ የትንሣኤያችን ምሳሌ ነው።
- **ፍልፈል፡-** በተወለደ በሰባተኛው ወር ይሞታል እንደገናም ይነሣል።
- **ጸጉር፡-** እየላጩት ያድጋል፤ ጥፍር እየቆረጡት ይተካል፤ ይህም የሰው ልጆች የመሞትና ዳግም የመነሣት ምሳሌ ይሆናል።

## 6.5 በብሉይ ኪዳን የነበሩ ትንሣኤን እንዴት ያያሉ?

ውድ ተማሪያችን ከላይ እንደተመለከትነው ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን በብዙ ምሳሌና ትንቢቶች የተጠቀሰ መሆኑን ተመልክተናል። በብሉይ ኪዳን የነበሩ አንዳንድ ሰዎችና ነገዶች ለትንሣኤ ሙታን የነበራቸውን አስተሳሰብና ግምት እንደሚመለከተው እንመለከታለን።

**ሀ. አይሁዳውያን፡-** ትንሣኤ ሙታንን የማያምኑ፣ የሰው ሕይወት በዚህች ምድር የሚያበቃ ነው ብለው የሚያስቡ፣ እንብላ እንጠጣ ነገ እንሞታለን የሚሉ ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስም ስለ እነርሱ ሲናገር፡- ‹‹ነገ እንሞታለንና እንብላና እንጠጣ›› 1 ቆሮ፡-15÷33 ከሚሉት እንድንሸሽ ይመክረናል።

**ለ. ሣምራውያን፡-** የነፍስን መነሣት ያምናሉ የሥጋን መነሣት ግን አያምኑም። *ሥጋ* አፈር ትቢያ ሆና ትቀራለች፤ ነፍስ ግን ወደ ፈጠራት ወደ አምላክ ትሔዳለች የሚሉ ናቸው። ስለ ነፍስም ሲናገሩ *‹ነፍስ እንደ ነፋስ እንደ ነጎድጓድ ያለች ናት›* ይላሉ።

**ሐ. ፈሪሳውያን፡-** ትንሣኤ ሙታንን ያምናሉ፤ ሲያምኑ ግን የቀደመው *ሥጋችን* አይነሣም፤ በአዲስ *ሥጋ* ከሰማይ አምጥቶ ያስነሣናል። ከዚያም በኋላ ማግባት መጋባት፤ መውለድ መዋለድ ይኖራል ብለው የሚያምኑ ናቸው።

**መ. ሰዱቃውያን፡-** ትንሣኤ ሙታን የለም መንፈስ፤ መላእክት፣ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚባሉት ሁሉ እንደሌሉ የሚያምኑ ናቸው፤ በአይሁድም ዘንድ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ነበሩ። በወንጌልም ላይ ከፈሪሳውያን ጋር ተከራክረው እንደገና ጌታችንን ስለ ትንሣኤ ሙታን በመከራከር የሚታወቁ ናቸው። ማቴ፡-22÷23፤ ማቴ፡-14÷3-5

ውድ ተማሪያችን በዚህም ዘመን ያሉ የእምነት ድርጅቶች በትንሣኤ ሙታን ላይ ያላቸው አመለካከት ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን አመለካከት የማይለይ ነው፤ ምድር ገነት ትሆናለች፣ መውለድ መዋለድ ይቻላል፣ ምድራዊ ሥርዓት በሰማይም እንዳለ የሚናገሩ ብዙ ሰዎችን አይተናል።

## 6.6 በምን ዓይነት ሁኔታ እንነሣለን?

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው የሰው ልጆች አነሣስ እንደ ፈሪሳውያን፣ እንደ ሰዱቃውያን ወይንም ሌሎች የእምነት ድርጅቶች እንደሚያስቡት አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ እንደተናገረ፡- *‹‹ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ይህንን እላለሁ፡- ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉምና፤ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስምና››* 1 ቆሮ፡-15÷50 ቅዱስ ጳውሎስ ይህ *ሥጋዊ* ደማዊ አካል እስከ መበስበስ ባሕርይው የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርስ ተናግሮአል።

ታዲያ ሰዎች በዕለተ ምጽአት አዲስ *ሥጋ* ይለብሳሉ ማለት ነው? ቢባል አይደለም ምክንያቱም የሰው ፍጥረት ሲነሣ የራሱን አካል ይዞ ነው የሚነሳው፤ ልዩነቱ የማይበሰብስና የማይሞት አካል ሆኖ መነሣቱ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን

ሲያስረዳ *‹‹ነገር ግን ሰው፡- ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል። አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም…››* 1 ቆሮ፡-15÷35 በማለት ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉትንና በሌላ አካልና ሥጋ ይነሣል የሚሉትን ከወቀሰ በኋላ በምን ዓይነት አካል እንደሚነሡ ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል፡- *‹‹የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲህ ነው፡- በመበስበስ ይዘራል፣ ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል፣ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፣ በኃይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፣ መንፈሳዊ አካል ይነሣል››* 1 ቆሮ፡-15÷42-44 በማለት ሰዎች በፍጥረታዊ አካላቸው ቢሞቱም ሲነሡ በመንፈሳዊ አካላቸው እንደሚነሡ ያሳውቀናል። ይህም ማለት ጻድቃን፡-

- በክብር እና በብርሃናዊነት ይነሣሉ ማቴ፡-13÷43፣ 1 ቆሮ፡-15÷43፣ ፊል፡-3÷21
- እንደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዝግ በሆኑ ነገሮች ማለፍ መቻል ዮሐ፡-20÷19፣ ሉቃ፡-24÷36፣ 1 ዮሐ፡-3÷2 *‹‹እርሱን እንድንመስል እናውቃለን››*
- ፍጥነትንና ኃይልን ማግኘት፡- ፍጥነት እንደመላእክት መንቀሳቀስ መቻል ነው። 1 ቆሮ፡-15÷43
- ስለ ብዙ ነገር ባለ ዕውቀት መሆን ሉቃ፡-16÷25፣ 1 ቆሮ፡-13÷12
- በኢየሩሳሌም ሰማያዊት በክብርና በዘለዓለማዊ ደስታ መኖር ሮሜ፡-8÷17፣ ራእ፡-21÷1—7
- ከመላእክት ጋር ማመስገንና ማወደስ ራእ፡-7÷9—12፣ ራእ፡-19÷1—7
- እግዚአብሔርንና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ፊት ለፊት ማየትና ከእነርሱ ጋር መኖር ራእ፡-21÷3፣ 1 ዮሐ፡-3÷2

ውድ ተማሪያችን ጻድቃን በክብርና በደስታ ለዘለዓለም በሕይወት ሲኖሩ ኃጥአን ደግሞ ለዘለዓለም በመከራና ስቃይ በገሃነመ እሳት ውስጥ ለሰይጣንና ለሠራዊቱ ወደ ተዘጋጀው የአሣር ቦታ ይወሰዳሉ። *‹‹በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፡- እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ሒዱ››* ማቴ፡-25÷41 ይላቸዋል፤ በዘለዓለማዊ መከራና ስቃይ ይኖራሉ ማለት ነው።

እኛንም ሁላችንን የቤተክርስቲያን ልጆች የሆነውን ሁሉ *‹‹… እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥቴን ውረሱ›› ማቴ፡-25÷34* የሚለውን የሕይወት ቃል ያሰማን፤ አሜን!



# መልመጃ ስድስት

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ ስጡ

1. ትንሣኤ ሙታን የሚለው ቃል ትርጉሙ ምን ማለት ነው?

   _____

   _____

2. ስንት የትንሣኤ ዓይነቶች አሉ? በዝርዝር በማብራራት አስረዱ።

   _____

   _____

3. ሙታን በምን ዓይነት አካልና አነሣስ ይነሣሉ?

   _____

   _____

4. በብሉይ ኪዳን ትንሣኤ ሙታን የለም ከሚሉት መካከል ሦስቱን ጥቀሱ?

   _____

   _____

5. ሙታን እንደሚነሡ በብሉይ ኪዳን ከተነገሩት ጥቅሶች መካከል በመጥቀስ አብራሩ?

   _____

   _____

# ማጠቃለያ

✞ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ለቤተክርስቲያን ትምህርት መሠረት የሆኑና እነዚህን አለማወቅ ራስን ለፈተናና ለዲያብሎስ ጸር አሳልፎ መስጠት ነው።

✞ ምሥጢረ ሥላሴ ስለ ሥላሴ አንድነትና ሦስትነት የምንረዳበት ነው። እግዚአብሔር አንድነቱ ሦስትነቱን ሳይጠቀልለው፤ ሦስትነቱ አንድነቱን ሳይከፋፍለው ጸንተው ለዘለዓለም የሚኖር አምላክ ነው።

✞ ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው እኛን የሰው ልጆችን ለማዳን በፍጹም ፍቅሩ ስለወደደንና ስላፈቀረን ነው።

✞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከፍጥረታት ተለይታ አምላክን ለመውለድ የበቃችና የተመረጠች ናት፤ ስትወልደውም በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወለደችው ፤ በዚህም እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ ብለን እንጠራታለን።

✞ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሲሆንም በፍጹም ተዋሕዶ ያለመለያየትና ያለመቀላቀል፤ ሥጋ የመለኮትን ባሕርይ ሳይጠቀልል፣ መለኮትም የሥጋን ባሕርይ ሳያጠፋ፤ በአንድነትና በተዐቅቦ፤ መለኮትና ሥጋ አንድ ሆነዋል። ለዚህም ነው ቅድስት ቤተክርስቲያን ከሁለት አካል - አንድ አካል፤ ከሁለት ባሕርይ - አንድ ባሕርይ በማለት የምታምነው።

✞ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ኃጢአት እና በደል ሳይኖርበት የእኛን ጥምቀት በጥምቀቱ ለመቀደስ ሲል በባሕረ ዮርዳኖስ፣ በዕደ ዮሐንስ በ30 (ሠላሳ) ዘመኑ ተጠመቀ። እኛም በጥምቀት ዘለዓለማዊ ሕይወትና የእግዚአብሔርን ልጅነት ለማግኘት ጥምቀትን አንዲት ጊዜ እንጠመቃለን። ኤፌ፡-4÷5፣ ማር፡-16÷16፣ ማቴ፡-28÷18

✞ ሙታን ሁሉ በዕለተ ምጽአት ይነሣሉ፤ ሁሉም እንደየሥራው መጠን በልዑል እግዚአብሔር ፊት ይቆማል። እኩሌቶቹ ለዘለዓለም ሕይወት ሲነሡ እኩሌቶቹ ደግሞ ለዘለዓለም ጉስቁልናና መከራ ይነሣሉ፤ ስንነሣም በማይሞትና በማይበሰብስ አካል እንነሣለን፤ ከዚያም በኋላ ምድራዊ ሥርዓት አይኖርም።



# ግለ- ፈተና (ራስን የመመዘኛ )ጥያቄዎች

## ትእዛዝ አንድ፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብበው ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐስት በማለት መልሱን በተሠጠው ባዶ ቦታ ላይ ያስፍሩ

1. አዕማደ ምሥጢር - ‹ምሥጢር› መባላቸው ከማያምኑ የተሰወረና የተደበቀ ስለሆኑ ነው።
2. ሥላሴ በስም፣ በአካል፣ በግብር እና በኩነት ሦስት ናቸው።
3. ሙታን በዕለተ ምጽእት በሚነሡብት ጊዜ የቀደመ ሥጋቸው በስብሳ ስትቀር በአዲስ አካል ይነሣሉ።
4. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በውኃ የተጠመቀው ውኃ በሁሉም ሥፍራ ስለሚገኝ እና ጥምቀትም ለሁሉም (ለሕዝብም ለአሕዛብም፤ ለድሃም ለሀብታምም) እኩል የምትፈጸም መሆኗን ለማመልከት ነው።

## ትእዛዝ ሁለት፡- በ‹ሀ› ክፍል የተዘረዘሩትን በ‹ለ› ክፍል ከተዘረዘሩት ጋር በማዛመድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ትክክለኛውን መልስ ይጻፉ

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| .....5. በመለኮት በአገዛዝ በህልውና | ሀ. ቅድመ ዓለም |
| .....6. የሥላሴ ልጅነት የምታሰጥ | ለ. ምሥጢረ ጥምቀት |
| .....7. የወልድ ልደት ከአብ መወለድ | ሐ. የሥላሴ አንድነት |
| .....8. ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ | መ. ምሥጢረ ቁርባን<br>ሠ.ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ምሣሌ |
| .....9. ፀሐይና ጨረቃ | ሰ. ምሥጢረ ተዋሕዶ |

# የመልመጃ እና ግለ- ፈተና (ራስን የመመዘኛ) ጥያቄዎች መልስ

## መልመጃ አንድ

1 ምሥጢር የሚለው ቃል ***ኦመሥጠረ (ኦመሠጠረ)*** ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙ ሰወረ ፣ደበቀ ፣ አረቀቀ ማለት ነው። ምሥጢር በሁለት ይከፈላል እነርሱም የፈጣሪ ምሥጢርና የፍጡራን ምሥጢር በመባል የታወቃሉ።

2 አዕማድ ማለት ምሰሶዎች ማለት ነው። በነጠላ ስንመለከተው ደግሞ አምድ ይሆናል ትርጉሙ ምሰሶ ቋሚ ማለት ነው። የምሰሶ ጥቅሙ አንድን ቤት አፅንቶ ማቆም ነው። አዕማደ ምሥጢራትም አንድን ክርስቲያን በሃይማኖቱ አፅንተው የሚቆሙ ናቸውና አዕማድ ተባሉ። **አንድም** ዐምድ ለጽሕፈት ሲሆን ደግሞ ለገጽ ስፋት መክፈያነት ያገለግላል። ለንባብ መመጠኛ ነው እንዲሁ ባሕርየ ሥላሴን ከመጠን አልፈን እንዳንመረምር የሚገድብ በመሆኑ የተሰጠ ስያሜ ነው።

3

- የመጀመሪያው ለማያምኑ የማይነገር (የተሰወረ) ምሥጢር ስለሆነ ነው።
- ሁለተኛው ደግሞ በሥጋዊ አእምሮ ተመራምሮ ስለማይደረስባቸው ነው። አዕማደ ምሥጢራትን ለማወቅና ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጸጋ ያስፈልጋልና
- የምናቃቸው ራሱ እግዚአብሔር የገለጠልን ያህል ስለሆነ ነው።

4.

- ምሥጢረ ሥላሴ፣ ምስጢረ ሥጋዌ፣ ምሥጢረ ጥምቀት፣ምሥጢረ ቁርባንና ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን ናቸው።

## መልመጃ ሁለት

1 የሥላሴ አንድነት በባህርይ፣ በመለኮትና በአገዛዝ ነው።

- **በባህርዩ፡** (ለባህርዩ መነሻ ምክንያት የለውም የገዛ ራሱ ለራሱ ባህርይ ነው) እግዚአብሔር ባህሪው ቅዱስ ነው ስንል አብ ቅዱስ ነው ወልድ ቅዱስ ነው መንፈስ ቅዱስ ነው ማለት ነው።
- **በመለኮት፡** አምላክነት መፍጠርን መግዛትን በፈቃድ አንድ መሆንን የሚገልጽ ነው አባ ሕርያቆስ ሲናገር መለኮትስ ማለት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው በማለት ተናግሯል
- **በአገዛዝ፡** በአራቱ መአዘን ሙሉእ በመሆን መግዛት ማለት ነው። የሥላሴ ሦስትነታቸው ወይም ሦስት መሆናቸው በስም፣ በአካል ግብር እና በኩነት ነው።

2

የሥላሴ አካል የማይታይ፣ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ ነው። አካላቸው ምሉዕ፣ ረቂቅ፣ ስፉሕ ነው እንጂ። ምሉዕነታቸውና ረቂቅነታቸው እንደምን ነው? ቢሉ፡-

**ምሉዕነታቸው፡**ከአርያም በላይ ቁመቱ፣ ከበርባሮስ በታች መሠረቱ፣ ከአድማስ እስከ አድማስ ስፋቱ፣ ተብሎ አይነገርለትም፤ አይመረመርም። ሥላሴ ዓለሙን ይወስኑታል እንጂ ዓለሙ ሥላሴን አይወስነውም። **ረቂቅነታቸው፡-**እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ስለዚህ መንፈስ ማለት የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ የማይያዝ ማለት ነው። እንኳን እግዚአብሔር እርሱ የፈጠራቸው መላእክት፣ የሰው ነፍስ፣ ረቂቃን ናቸው። ታዲያ ይህ የማይታየው የማይጨበጠው የሥላሴ አካል በተከፍሎ ልዩ በሆነች ሦስትነት የጸና አካል ነው። ይህ ማለት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የራሳቸው የሆነ ገጽ አካል አላቸው ማለት ነው።

3 እግዚአብሔርም አለ ሲል "አለ" የሚለው ቃል አንድነቱን ሲገልጽ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር ሲል ደግሞ "በመልካችን" "ምሳሌያችን" ና "እንፍጠር" የሚሉት ቃላት ሦስትነቱን ይገልጻሉ።

# መልመጃ ሦስት

1) እግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት አሉት እነርሱም ቅድመ ዓለም ከአብና ድህረ አለም (5500ዘመን በኋላ) ከእቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ነው።

2) **የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የስሟ ትርጓሜ** *መርሕ ለመንግስተ ሰማያት ማለት ነው ፣ ጸጋ ወሐብት* ማለት ነው፣ እመቤታችን በዕብራይስጥ ቋንቋ *ማሪሃም* ትባላለች፣*ማሪ* ማለት እመቤት ማለት ነው *ሃም* ማለት ደግሞ ብዙሐን ማለት ነው በዕብራይስጥ ማሪሃም ማለት የብዙሐን እመቤት ማለት ነው። **ማ** ፡ ማኅደረ መለኮት / የመለኮት ማደሪያ/ **ር** ፡ ርግብየ ይቤላ **ያ** ፡ ያንቃአዱ ሐቤኪ ኩሉ ፍጥረት በአንቺ አማላጅነት ያመኑ ሁሉ ቅድስት ሆይ ለምኝልን እያሉ ወደአንቺ ይለምናሉ ማለት ነው። **ም** ፡ ምሰአል ወምስጋድ ወመስተሥርዬ ኃጢያት ኃጥያትን ለማስተስረይ ምሕረትን ከፈጣሪ እያማለድሽ የምታሰጪ ማለት ነው፡ ፡

3)

- **የኖህ መርከብ፡** እግዚአብሔር ኖህን ከጥፋት ውሃ እንዲድን መርከብን እንዲሰራ አዞት ነበር ሦስት ክፍል ያላት መርከብ ሰርቶ ኖህና ቤተሰቦች ከጥፋት ውሃ ድነዋዋል።እመቤታችንም ቅድስት ድንግል ማርያም የኖህ መርከብ ትባላለች፣ የኖህ ቤተሰቦቹ ከጥፋት የዳኑት በመርከበዋ ውስጥ ገብተው ነው፤ እኛም ከጥፋት ከገሀነም እሳት ለመዳን በእመቤታችን አማላጅነት መተማመን ወደ እርሷ መጠጋት ያስፈልጋልና።
- **የያዕቆብ መሰላል፡** ያዕቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ተጣልቶ በካራ ሲሄድ ደክሞት ተኛ በህልሙ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ተዘርግቶ መላዕክት ሲወጡበት ሲወርዱበት ተመለከተ በመሰላሉ ላይ እግዚአብሔር ተቀምጦ ነበር። ያዕቆብም ከህልሙ ነቃ ያንን ቦታ ቤቴል ብሎ ጠራው የእግዚአብሔር ቤት ማት ነው፤እመቤታችን የያእቆብ መሰላል ትባላላች። መሰላሏ ከምድር እስከ ሰማይ ደረሶ ነበር በእመቤታችን አማካኝነት ምድራውያን ሰዎች ከሰማውያን መላእክት ጋር ታርቀዋልና። በመሰላሉም መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ነበር እመቤታችን ጌታችን በወለደችው ጊዜ ለመስጋና ለብስራት መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ነበር
- **ጌዲዮን ጸምር**፡ እስራኤላውያንን ከምድያማውያን ነጻ እንደሚያወጣቸው መልአኩ ነገረው። ጌዲዮንን እግዚአብሔር ህዝቡን እኔ የማዳን እንደሆነ ይህንን እይ አለው። በበግ ጠጉር የተሰራች ጸምር (ምንጣፍ) ላይ ጠል (ዝናብ) ይውረድ መጸምሯንም ይንካ ሌላውን አይንካ አለው ዝናብ ዘነበ ምንጣፏን ነካ ሌላው ቦታ ደረቅ ሆነ፤ እንደገና ጠል ሆነ ሌላውን ቦታ ሲረጥብ ጸምሯ ግን ደረቀች። እመቤታችን በጌድዮን ጸምር መመሰሏ ዝናቡ (ጠጡ) ምንጣፏን ብቻ መንካቱ ሌላው ቦታ መድረቁ፤ ከሌሎች ሴቶች (ከፍጥረታት) ሁሉ ለይቶ በእመቤታችን ማደሩን፤ ሌላው ቦታ ዝናብ (ርጥብ) ሆኖ ጸምሯን አለመንካቱ ኃጢያት በሰው ዘር ሁሉ ላይ ሲነግስ እመቤታችን ግን የአዳም ውርስ ኃጢያት እንዳልነካት እርሷን ለይቶ እንዳስቀመጣት ማወቅ ይችላል

4)

- ‹‹እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና ማደሪያውምትሆነው ዘንድ ወዷአታልና እንዲህ ብሎ ይህች የዘላለም ማረፊያዬ ናት መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ›› መዝ 131÷13 እመቤታችን እግዚአብሄር አምላክ ከማንም በላይ እንደመረጣት እናቱም እንደምትሆን ለዘላለም ማደሪያው እንደሆነች ተናግሯል።
- ነቢዩ ኢሳይያስ ‹‹ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች›› ኢሳ 7÷14 በማለት እመቤታችን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና እንደምትወልድ ተናግሯል።

5)

- *ለሰው ልጆች ያለው ፍጹም ፍቅር ለመግለጽ፡* እኛን የሰው ልጆችን ምንኛ እንደወደደን ለመግለጽ እኛም ፍቅሩን እንድንረዳ ሲል ነው የእኛን ባህርይ ባህርዩ እስከ ማድረግ እኛን እራሳችንን ሆኖ ሰው ሆኖ ተገልጿል።
- *ለኣርኣያ ለኣብነት፡* (የሰው ልጆች መስራት ያለባቸውን ሰርቶ ለማሳየት )
- *ለካሳ ለቤዛ፡* ቀዳማዊው አዳም አትብል የተባለውን በመብላት አምላክነትን በመመኘት ሞትን አመጣ
- *የሠይጣንን ጥበብ በመለኮታዊ ጥበቡ ለመሻር፡* ሰይጣን በእባብ ተሰውሮ አዳምና ሔዋንን አሳስቶአቸዋል ሰይጣን በጥበቡ እንዳሳተቸው ይህንን የሠይጣንን ጥበብ ለመሻር አምላክ ሰው ሆኗል።

6) ተዋሕዶ ማለት በተገናዝቦ አንድ ሆነ ምንታዌነትን(ሁለት መሆንን) አጠፋ ማለት ነው ይህም ተዋሕዶ አንድ ሆነ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙ አንድ መሆን ከሁለት ባህርይ አንድ በሕርይ ከሁለት አካል አንድ አካል ማለት ነው።ይህም በተአቅቦ (በመጠባበቅ) ነው መለኮት የሥጋን ባሕርይ ሳያጠፋ፤ሥጋም የመለኮትን ባሕርይ ሳያጠፋ በመጠባበቅ ማለት ነው።ይህም ይህ ለመለኮት ይህ ለሥጋ ሳይባል በአንድ አካል በአንድ ባሕርይ መገኘት ማለት ነው።

## መልመጃ አራት

1.ጥምቀት፡ ‹አጥመቀ› አጠመቀ ካለው የግእዝ ግሥ የወጣ ነው። ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ በተጸለየበት ውኃ ‹ማየ ገቦ/ ማየ ሕይወት› ውስጥ በሥላሴ ስም መጥለቅ፣ መዘፈቅ፣ መነከር ማለት ነው።

2.ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠላሳ ዘመኑ፣ በዮሐንስ እጅ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቋል። ቅዱስ ዮሐንስ ያጠምቅ የነበረው የንስሓ ጥምቀትን ነበር፤ ጌታችን በእርሱ እጅ የተጠመቀው በደል ኖሮበት ይቅርታን ፈልጎ ሳይሆን በጥምቀቱ ጥምቀታችንን ሊያከብርልን አንድም ጌታው ከተጠመቀ ሎሌውም ይጠመቃልና እርሱ እንደተጠመቀ እኛም እንድንጠመቅ አብነት ወይም ምሳሌ ሊሆነን ነው።ጌታ ዮሐንስን ወደ እኔ ዝንድ መጥተህ አጥምቀኝ ሳይል እራሱ ወደ ዮሐንስ ዘንድ ሄዶ መጠመቁ አንድም ለትህትና ሲሆን ሌላው ደግሞ ሥርዓትን ሲደነግግልን ነው። ጌታ ዮሐንስን መጥተህ አጥምቀኝቢለው ኖሮ የዛሬ ነገሥታት መኳንንትና ታላላቅ ሰዎች ካህናትን ቤተ መንግሥታችን ወይም ቤታችን ድረስ መጥታችሁ ልጆቻችንን አጥምቁ ባሉ ነበር። ይህን እንዳይሉ ጌታ እራሱ አርአያ ስለሆነ እነሱም አይሉም ቢሉም ቤተክርስቲያን አትቀበለውም።

3. አብነት ለመሆን፣ የዕዳ ደብዳቤያችንን ለመደምሰስ ፣ በምሳሌ ብቻ ይታወቅ የነበረውን ምሥጢረ ሥላሴ ለመግለጥ

4.በ30 አመቱ የተጠመቀው፡-

- 30/ሠላሳ/ ዘመን ሙሉ ሰው የሚሆኑበት ለምግባር ለትሩፋት የሚበረቱበት በመሆኑ በ30/ሠላሳ/ ዘመኑ በመጠመቅ ጥምቀትን የሥራው መጀመሪያ አደረገ፤ እርሱ ሊቀካህናት፣ መመህርና አዳኝ ነውና።
- የቀደመው ሰው አዳም የ30/ሠላሳ/ ዘመን ጎልማሳ በመሆን ተፈጥሮ ልጅነትን አግኝቶአል፤ መልሶ ይህን ልጅነት በኃጢአት ምክንያት አጥቶታል፤ ዳግማዊ አዳም ጌታችንም በ30/ሠላሳ/ ዘመኑ ተጠምቆ የአዳምን የልጅነት ጸጋ መልሶለታል።

በዮርዳኖስ የተጠመቀው፡-

- በዮርዳኖስ ተጥሎ የነበረውን የዕዳ ጽሕፈት ለመደምሰስ
- ትንቢትና ምሳሌን ለመፈጸም

5.

- ራሱ ጌታችን በውኃ ተጠምቋልና
- ትንቢተ ነቢያት ይፈጸም ዘንድ
- ጌታችን በውኃ እንድንጠመቅ ስላዘዘን
- ሐዋርያት በውኃ አጥምቀዋልና
- ንጉሥ ፈርያን በውኃ ድል እንደተነሣ በውኃ ተጠምቀንና የእግዚአብሔር ልጆች ተሰኝተን ኃጢአትን ሁሉ ድል እንደምንነሣ ለማመልከት
- የቀድሞ ሰዎች በውኃ ጥፋት ደርሶባቸው ነበርና ውኃ ለምሕረት መፈጠሩን ይጠራጠሩ ነበር፤ ማለትም ለመርገም ብቻ እንደተፈጠረ አድርገው ያስቡና ያምኑም ነበር። ውኃ ለምሕረትም መፈጠሩን ለማመልከት
- ውኃ መንጽሔ እድፍ ነው፤ ማለት ከእድፍ ያነጻል፣ ያጠራል፤ በጥምቀትም ከነፍስና ከሥጋ ገርስቋልና እንደምንጠራ፣ እንደምንነጻም ለማመልከት
- ውኃ በሁሉም ቦታ ይገኛል፣ ለድሃም ለሀብታምም እኩል ነው። ጥምቀትም ለሁሉም (ለሕዝብም ለአሕዛብም፤ ለድሃም ለሀብታምም) እኩል የምትፈጸም መሆኗን ለማመልከት
- ውኃ መልክን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፤ እኛም በውኃ ተጠምቀን የሥላሴን መልክ በመንፈስ እናያለንና

- እሳት ምንም ያህል ቢበረታ በውኃ ይጠፋል፤ እኛም በውኃ ተጠምቀን አስፈሪ ከሆነ ከገሀነመ እሳት እንድናለን ስንል ማር፡-16፣16
- ውኃ ያለመልማል፤ እኛም በውኃ ተጠምቀን የሥጋና የነፍስን ልምላሜ እናገኛለን ስንል
- ውኃ ውኂዝ (ፈሳሽ) ነው፤ በዚህም ምክንያት ከአጽናፍ አጽናፍ ይደርሳል፤ ጥምቀትም በሁሉ ያለች መሆኗን ለማመልከት
- ውኃ ተዋስያን(ጥቃቅን ነፍሳት) አይቀርቡትም፤ በውኃ ጥምቀት ሰውነቱ የከበረ የመንፈስቅዱስ ማደሪያ ርከርሳት መናፍስት አይቀርቡትምና ነው።

6.

የመጀመሪያው ሰው አዳም ወደ ገነት በ40ኛው ቀን ሔዋን ደግሞ በ80ኛው ቀን ገብተዋል። ኩፋ፡-4፣9 ‹በተፈጠረባት ምድር ለአዳም አርባ ቀን ከተፈጸመለት በኋላ ይገዛትም ይጠብቃትም ዘንድ ወደ ገነት አስገባነው፤ ሚስቱንም በሰማንያ ቀን አስገባናት› ሕፃናትም እንደየጸታቸው ወንዶች በተወለዱ በዐርባ ቀናቸው ሴቶችም በሠማንያ ቀናቸው ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃቸው ጥምቀት ይፈጸምላቸዋል።

የኦሪትን ሕግና ሥርዓት መሠረት በማድረግ ዘሌ፡-12፣1-8 ‹ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅንም ብትወልድ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት፤ እንደ ሕመምዋ መርገም ወራት ትረክሳለች። በስምነተኛው ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ። ከደምዋ እስክትነጻ ሠላሳ ሦስት ቀናት ትቀመጥ (ሰባትና ሠላሳ ሦስት ዐርባ መሆኑን ያስተውሉ) ። ሴት ልጅም ብትወልድ እንደመርገምዋ ወራት ሁለት ሣምንት ያህል የረከሰች ናት፤ ከደምዋም እስክተነጻ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ (ሁለት ሣምንት ማለት ዐሥራ ዐራት ቀናትና ስድሳ ስድስት ቀናት ሠማንያ ቀናት ይሆናሉ)።

7. ትምህርት ፣ እምነት ፣ ንስሓ። በተጨማሪም አንድ ንዑሰ ክርስቲያን ከመጠመቁ በፊት ለሦስት ዓመት ያህል በማኅበር ጸሎት ይካፈላል፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ይማራል፣ ንስሓውን ወይም ቀኖናውን ይፈጽማል። ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ ይጠመቃል።

8.

- ምክንያቱም ሰው ከእናት ከአባቱ አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚወለድ ከእግዚአብሔርም አንድ ጊዜ በጥምቀት ይወለዳል።
- የቃለ እግዚአብሔር ምስክርነት ኤፌ፡-4፣5 ‹አንድ ጌታ፤ አንዲት ሃይማኖት፤ አንዲት ጥምቀት› ፤ ‹ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል› ማር፡-16፣16

## መልመጃ አምስት

1) መሥዋዕት ያቀርብ የነበረው መልከጼዴቅ ሲሆን በኅብስትና በወይን ያቀርብ ነበር
2) ‹መታሰቢያዬ› ማለቱ ግን ቅዱስ ቁርባኑን በተቀበልን ጊዜ ሁሉ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሠጠንን እርሱን ጌታችንን ማሰብ እንዲገባን ያስረዳል። ቅዱስ ጳውሎስ ሰንዲህ ብሎ እንደተናገረ፡- ‹ይህን እነጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ይህንንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና› 1 ቆሮ፡-11፣26
3)

- ቅዱስ ቁርባን በስንዴ/ኅብስትና በወይን ከሆነበት ምሥጢርና ምክንያት አንዱ ትንቢተ ነቢያትን ለመፈጸም ነው።
- መልከጼዴቅ በኅብስትና በወይን መሥዋዕት ያቀርብ ነበርና ያንን ምሳሌ ለመፈጸም ነው። ዘፍ፡-14፣17-20
- ጌታችንም ራሱን በወይን መስሎ ተናግሮአል። ዮሐ፡-15፣1 ‹እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ›
- ጌታችንም ከእናቱ ከእመቤታችን ጋር ሲመገቡት የኖሩት ነውና በእውነት ሥጋውንና ደሙን መሥጠቱን ለማመልከት **አንድም** ስንዴ ስብ/ሥጋ ይመስላል ወይንም ደም ይመስላልና በሚመስል ነገር ለመሥጠት አንድም ስንዴ ልባም ሴት የየዘችው እንደሆነ ነውር የሌለበት የማይለወጥ ይሆናል (ነውር የሌለባት የማትለወጥ ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል)
- ወይንንም ቢጥሉት ከዕለት ዕለት ኃይሉ እየጨመረ ይሔዳል (ኃይል የሚሆን ሕግ ሠራሁላችሁ ሲል) በኅብስታና በወይን ሆኗል።

4)

- አዳም አባታችን በለስን በመብላት በመብል ጠፍቶ ከገነትም ወጥቶ ነበርና በወጣበት ነገር እንዲገባ በጠፋበት ነገር እንዲድን ለማድረግ (ዮሐ፡-6፣54)፡፡
- መብል ከሰውነት ይዋሐዳልና በጸጋ ተዋሕጃችሁ እኖራለሁ ለማለት፡፡
- መብል መጠጥ ያፋቅራል ቅዱስ ቁርባንም የጌታችንን ፍቅር በልቡና ያሳድራልና፡፡
- የተራበን የተጠማን ሰው ቢያበሉት ቢያጠጡት ይወድዳልና በነፍስ ለተራብን ለእኛ ምግበ ነፍስ ይሆነን ዘንድ ቅዱስ ቁርባንን በመብልና በመጠጥ አድርጎታል፡፡

## መልመጃ ስድስት

1. ትንሳኤ ሙታን ማለት ነፍስና ሥጋ ተለያይተው ከኖሩበት እንደገና ተዋሕደው በእለተ ምጽአት የሚነሱበት ወይንም ከሞት በኋላ ነፍስና ሥጋ በእንደገና ተዋሕደው የሚነሱበት ምሥጢር ማለት ነው፡፡
2. ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን የሆነችው የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የሰው ልጅ ሁለት አይነት ትንሳኤዎች እንዳሉት ታምናለች እነሱም **ትንሳኤ ልቡና** እና **ትንሳኤ ዘጉባኤ** በማለት የሚታወቁ ናቸው፡፡

- ***ትንሳኤ ልቡና፡*** ትንሳኤ ልቡና ማለት የሰው ልጅ በሕይወቱ እያለ በኃጥያት ባርነት፣በክፋትና በበደል ውስጥ በሞኖር ከእግዚአብሔር በመለየት የሚኖረውኑሮ ሞት ስለሆነ ከዚያ የሚነሳበት ወይም የሚወጣበት ትንሳኤ ትንሳኤ ልቡና በማለት ይታወቃል አንድም ከመነሳታችን በፊት በንስሐና በጽድቅ አሁን የምንነሳው ትንሳኤ ማለት ነው፡፡ ለዚህ ትንሳኤ ልቡና ንስሐ ጥምቀት እና ቁርባን ወሳኝ ናቸው፡፡
- ***ትንሳኤ ዘጉባኤ፡*** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማለት በመጨረሻው ቀን የሙቱት ሁሉም በአንድላይ በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ የሚነሱበት ማለት ነው ይህም እነ ነብዩ ኤልያስ ፣እነ ኤልሳ፣እለቅዱ ጳውሎስ ካስነሷቸው የሚለይ ነው ይህም ማለት የሰው ልጅ ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ አራቱ ባህርያት ከተለዩት ነፍሱም ከተለያዩ በኋላ በአንድ በመሰባሰብ የሚቁበት ማለት ነው ይሕም ኃጥአን ለመከራና ለአሳር ጻድቃን ለዘላለም ሕይወትና ጽድቅ የሚነሱበት ማለት ነው።

3.

- የሞትክ ሁሉ የሚል የአዋጅ ቃል በመላእክት አለቃ ሲነገር የሞቶት ሁሉ ካሉበት ተሰብስበው ይነሳሉ
- ***የመጀመሪያው መለከት ሲነፋ፡-*** አውሬ የበላው አፈር ትቢያ የሆነው በባህር ውስጥ የቀረው ሁሉ የራስ ቅል ባለበት ይሰባሰባል፡፡
- ***ሁለተኛው መለከት ሲነፋ፡-*** ሥጋና አጥንቱ በአንድ ላይ በመገጣጠም አንድ በመሆና ሳይንቀሳቀሱ ትኩስ በድን እሬሳ ይሆናሉ፡፡
- ***ሥስተኛው መለከት ሲነፋ፡-*** በአካል በምንናገርበት አንደበት ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው መብላት መጠጣት ማግባት በጋባት መዋለድ የማያስፈልገው ሞት የሌለበት ሆነው በጎም ሆነ ክፉ ስራቸውን ይዘው ጻድቃን ወደ ገነት ኃጥዓን ወደ ገሀነመ እሳት ይሄዳሉ፡፡

4.

- ***አይሁዳውያን፡-*** ትንሳኤ ሙታንን የማያምኑ የሰው ህይወት በዚህች ምድር የሚያበቃ ነው ብለው የማያምኑ እንብላ እንጠጣ ነገ እንሞታለን የሚሉ ናቸው፡፡
- ***ሳምራውያን፡-*** የነፍስን መነሳት ያምናሉ የሥጋን መነሳት ግን አያምኑም፡፡ ሥጋ አፈር ትቢያ ሆና ትቀራለች ነፍስ ግን ወደ ፈጠራት ወደ አምላክ ትሔዳች የሚሉ ናቸው፡፡
- ***ፈሪሳውያን፡-*** ትንሳኤ ሙታንን ያምናሉ ሲያምኑ ግን የቀደመው ሥጋችን አይነሳም በአዲስ ሥጋ ከሠማይ አምጥቶ ያሥነሳናል፡፡ ከዛም በኋላ ማግባት መጋባት መዋለድ ይቻላል ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡

5.

- ‹‹ሙታንህ ሕያው ይሆናሉ ሬሳዎችም ይነሳሉ ... ምድርም ሙታንን ታወጣለች›› ኢሳ 26÷19
- ‹‹በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘላልም ህይወት፤እኩሌቶቹ ወደ እረፍትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና›› ት.ዳን 12÷2

- ‹‹ጌታ እግዚአብሔርም ለእነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል እነሆ ትንፋሽን አገባባቸዋለው በሕይወት ትኖራላችሁ›› ሕዝ 37 ÷ 5
- ‹‹ሥጋዬ በተስፋ ታድራለች ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፣ቅዱስህንም መበስበስ ያይ ዘንድ አትተወውም›› መዝ 16÷9—10

**ግለ- ፈተና (ራስን የመመዘኛ)**

| | |
|---|---|
| 1. እውነት<br>2. እውነት<br>3. እውነት<br>4. እውነት | 5. ሐ<br>6. ለ<br>7. ሀ<br>8. ሰ<br>9. ሠ |



በዲ/ን ቢሊየን ግርማ
billiongirmay@gmail.com
16/11/2008 ዓ.ም

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!